# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ዓርብ

83ኛ ዓመት ቁጥር 291 ሰኔ 21 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









ፎቶ - ሃይሽ አብርሃ

# በአዲስ አበባ ነዳጅ ለመቅዳት ረጃጅም ወረፋዎችን ለመጠበቅ መገደዳቸውን አሽከርካሪዎች ተናገሩ

## - ችግሩ የተፈጠረው ጅቡቲ ያለው የነዳጅ ዴፖ እድሳት ላይ በመሆኑ ነው

ሳሙኤል ወንደሰን

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ ነዳጅ ለመቅዳት ረጃጅም ወረፋዎችን ለመጠበቅ መገደዳቸውን አሽከርካሪዎች ተናገሩ። የነዳጅና ኢነርጂ ባለሥልጣን በበኩሉ ችግሩ የተፈጠረው ጅቡቲ ያለው የነዳጅ ዴፖ እድሳት ላይ በመሆኑ መሆኑን አስታውቋል።

ነዳጅ ለመቅዳት ተሰልፈው ያገኘናቸው አቶ አማረ በላይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ በአዲስ አበባ የተለያዩ አካባቢዎች አምስት ማደያዎች ላይ ነዳጅ ለመቅዳት ረጃጅም የመኪና ሰልፎች ተመልክተዋል። አራት ኪሎ ቱሪስት ሆቴል አካባቢ የሚገኝ የነዳጅ ማደያ ስፍራ በተመሳሳይ ነዳጅ ለመቅዳት የተሰለፉ መኪኖች ወረፋ በመኖሩ ነዳጅ ለመቅዳት ረጅም ጊዜ ለመጠበቅ መገደዳቸውንም ጠቁመዋል።

በአዲስ አበባ ነዳጅ ... ወደ ገጽ 11 ዞሯል

# የኮሪደር ልማቱ

## ቅርሶችን በማልማት በመዲናዋ የቱሪስት ፍሰት እንዲያድግ ዕድል ይፈጥራል

ታደሠ ብናልፈው

አዲስ አበባ፡- የኮሪደር ልማቱ ቅርሶችን በማልማት በመዲናዋ የቱሪስት ፍሰት እንዲያድግ ዕድል ይፈጥራል ሲል የአዲስ አበባ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ አስታወቀ፡፡

በየካ ክፍለ ከተማ ወረዳ አንድ የተከፈተውን ታሊስማን አዲስ የስዕል ጋለሪ አስመልክተው ንግግር ያደረጉት የአዲስ አበባ ባሕልና ቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ ሂሩት ካሣው (ዶ/ር)፤ የኮሪደር ልማት ቅርሶችን ደረጃቸውን ጠብቀው እንዲለሙ በማድረግ የመዲናዋ የቱሪስት ፍሰት እንዲያድግ ዕድል የሚፈጥር ነው፡፡

የኮሪደር ልማቱ በመዲናዋ አቧራ ለብሰው የሚገኙ ቅርሶች ደረጃቸውን ጠብቀው እንዲለሙ በማድረጉ ከተማዋን ከቱሪስት መዳረሻነት ወደ ተጎብኚነት አሸጋግሯታል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

አዲስ አበባ ከተማ ዓለም ላይ አሉ የተባሉ ቅርሶች የሚገኙባት ከተማ ብትሆንም የቱሪስት

የኮሪደር ልማቱ ... ወደ ገጽ 11 ዞሯል



ኬይረዲን ተዘራ (ዶ/ር)

# ወጣቶች የሀገራቸውን ብዝኃነት በመረዳት ለሀገራዊ ግንባታ ቁልፍ ሚና ሊወጡ ይገባል

- የአዲስ አበባ ከተማ የበጐ ፈቃድ አገልግሎት ማስጀመሪያ መርሐ ግብር ተካሄደ

ሞገስ ፀጋዬ

አዲስ አበባ፡- ወጣቶች የሀገራቸውን ብዝኃነት በመረዳት ለሀገራዊ ግንባታ ቁልፍ ሚና ሊወጡ እንደሚገባ ሠላም ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

የአንድ ወር የክረምት በጐ ፈቃድ አገልግሎት

ወጣቶች የሀገራቸውን ... ወደ ገጽ 11 ዞሯል

# በኦሮሚያ በዘንድሮው አረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር 4 ነጥብ 95 ቢሊዮን ችግኞች ይተከላሉ

ማርቆስ በላይ

ቄለም ወለጋ፡- በኦሮሚያ ክልል በ2016 ዓ.ም አረንጓዴ ዐሻራ መርሐግብር 4 ነጥብ 95 ቢሊዮን ችግኞች እንደሚተከሉ ተገለጸ።

የኦሮሚያ ክልል ርዕሰ መስተዳደር አቶ ሽመልስ አብዲሳ አረንጓዴ ዐሻራ ችግኝ ተከላ መርሐ ግብር “መርሐ ግብሩ የምትተክል ሀገር የሚያጸና ትውልድ” በሚል መሪ ሀሳብ በክልል ደረጃ በቄለም ወለጋ ዞን ላሎ ቂሌ ወረዳ ትናንት አስጀምረዋል።

ርዕሰ መስተዳድሩ መርሐ-ግብሩን ባስጀመሩበት ወቅት ባስተላለፉት መልእክት እንደገለጹት፤ በአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ-ግብር የተሠራውን ሥራ አጠናክሮ በማስቀጠል የደን ሽፋንን ማሳደግ ይገባል።

የለውጡ መንግሥት በአየር ንብረት ለውጥ ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮችን ለመከላከል እየሠራ እንደሚገኝ ጠቅሰው፤ የአፈር መሸርሸርን ለመቀነስ ለአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራ እንደሚገኝ ተናግረዋል።

ዘንድሮ ለመትከል ከታቀደው አንድ ነጥብ 29 ሚሊዮን ሄክታር መሬት ውስጥ 814 ሺህ ሄክታር መሬት ከሳተላይት ምስል ጋር የተናበበ እንዲሆን ተደርጓል ያሉት አቶ ሽመልስ፤ ከሚተከሉ ችግኞች ውስጥ 10 በመቶው



በኦሮሚያ በዘንድሮው ... ወደ ገጽ 11 ዞሯል




# በትምህርት ለትውልድ ንቅናቄ የሚደረገው ተሳትፎ እንዲጠናከር ጥሪ ቀረበ

## - በንቅናቄው እስካሁን 25 ቢሊዮን ብር ተሰብስቧል

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- በትምህርት ለትውልድ ንቅናቄ ሁሉም ባለድርሻ አካላት የሚያደርጉትን ተሳትፎ አጠናክረው እንዲቀጥሉ ትምህርት ሚኒስቴር ጥሪ አቀረበ፡፡ ከጥቅምት 2015 ዓ.ም ጀምሮ ለንቅናቄው 25 ቢሊዮን ብር ተሰብስቧል

የኢትዮጵያ መምህራን ማኅበር 11ኛውን ዓመታዊ የትምህርት ጥራት ጉባኤና 'የሕዝብ ፈንድ ለትምህርት' ዘመቻ ማስጀመሪያ መርሐግብር ትናንት አካሂዷል፡፡

በመርሐግብሩ ላይ በእንግድነት የተገኙት የትምህርት ሚኒስትር ዴኤታ ወይዘሮ አየለች እሸቴ እንደገለጹት፤ የትምህርት ጥራትን ለማሻሻል ከሚከናወኑ ተግባራት አንዱ የትምህርት ቤቶችን ደረጃ ማሻሻል ነው፡፡

ይህን ችግር ለውጥ በሚያመጣ መልኩ ለመቅረፍ በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ይፋ የተደረገውን የትምህርት ለትውልድ ንቅናቄ ተጠናክሮ ይቀጥላል ያሉት ወይዘሮ አየለች፤ መላው ኢትዮጵያውያንና ሁሉም ባለድርሻዎች በንቅናቄው ላይ በንቃት እንዲሳተፉ ጥሪ አቀርበዋል።

በሳይንስና ቴክኖሎጂ በልጽገው የምናያቸው ሀገራት የእድገታቸው ምስጢር ትምህርት ነው ያሉት ወይዘሮ አየለች፤ ትምህርት የሁሉም ነገር መሠረት ነው ካልን ደግሞ ለትምህርት ጥራት የሚያስፈልገውን አስተዋፅዖ ማበርከት ይኖርብናል ብለዋል።



ዮሐንስ በንቲ (ዶ/ር)



ወይዘሮ አየለች እሸቴ

ባለፉት ዓመታት ትምህርት ላይ የተሠሩ ጥናቶች ትምህርት ላይ ያለውን ስብራት አመላክተው፤ የትምህርት ስብራትን ለመጠገን መንግሥት የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ አዘጋጅቶ ተግባራዊ ለማድረግ ጥረት እያደረገ መሆኑንና ለውጤታማነቱ የመምህራንና ትምህርት አመራሮች ሚና ከፍተኛ መሆኑን አንስተዋል። መምህራን ከዚህ ካሪኩለም ጋር የበለጠ ትውውቅ እንዲኖራቸው ለማድረግ እየተሠራ ነው ሲሉ አስረድተዋል።

በትብብር ስንሠራ ለውጥ እናመጣለን ያሉት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ ለዚህም በ"ትምህርት ለትውልድ ንቅናቄ" ከተጀመረበት ጥቅምት 2015 ዓ.ም ጀምሮ 25 ቢሊዮን ብር መሰብሰብ መቻላችን ትልቅ ማሳያ ይሆናል ብለዋል።

በተገኘው ሀብት የአዳዲስ ትምህርት ቤቶች ግንባታ፣ ጥገናና የግብዓት ማሟላት ሥራዎች እየተከናወነ መሆኑን ጠቁመው፤ ከችግሩ ስፋት አንጻር አሁንም ብዙ ሥራ ይጠበቃል ሲሉ ተናግረዋል። የኢትዮጵያ መምህራን ማኅበርም ይህንን ንቅናቄ የሚደግፍ "የሕዝብ ፈንድ ለትምህርት" ዘመቻ ማስጀመሩ የሚበረታታና ትልቅ አቅም የሚፈጥር መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የኢትዮጵያ መምህራን ማኅበር ፕሬዚዳንት ዮሐንስ በንቲ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ የትምህርት ሥርዓቱ ችግር ላይ ለመሆኑ ብዙ ማሳያዎች አሉ ብለዋል።

የመምህራን ብቃት፣ የትምህርት ቤቶች ደረጃና የሐሰተኛ ትምህርት ማስረጃዎች ጥራቱ መውረድ ላይ ትልቅ አስተዋፅዖ እንዳላቸው አንስተዋል።

የትምህርት ጥራት በዓለም አቀፍ ደረጃ ትልቅ አጀንዳ መሆኑን አስታውሰው፤ ማኅበሩ የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅ የድርሻውን ሚና ለማበርከት የተለያዩ ተግራትን እያከናወነ መሆኑን ጠቁመዋል። "የሕዝብ ፈንድ ለትምህርት ዘመቻ" የዚህ አንዱ አካል ነው ሲሉ ተናግረዋል።

በትብብር ከተሠራ ለውጥ ማምጣት ይቻላል ያሉት ዮሐንስ (ዶ/ር) ፤ የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅ በሚሠሩ ሥራዎች ላይ ሁላችንም የየድርሻንን አስተዋፅዖ ማበርከት ይጠበቅብናል ብለዋል።

"የሕዝብ ፈንድ ለትምህርት" ዘመቻ ማኅበረሰቡ የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅ በሚሠሩ ሥራዎች ላይ ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርግ ያለመ ንቅናቄ ሲሆን፣ በቀጣይነት ትምህርት ቤቶችን ጨምሮ ሕዝቡን ተደራሽ በሚያደርግ መልኩ እንደሚከናወን ተጠቁሟል፡፡

# ወመዘክር

## ሰነዶችን በሕገወጥ መንገድ የሚያስወግዱ ተቋማትን ተጠያቂ እንደሚያደርግ አሳወቀ

### - ከ35 በላይ ተቋማት የሰነድ ይወገድልኝ ጥያቄ አቅርበዋል

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- አስፈላጊ ሰነዶችን በሕገወጥ መንገድ በራሳቸው አልያም በጨረታ የሚያስ ወግዱ ተቋማትን በሕግ አግባብ ተጠያቂ እንደሚያደርግ የኢትዮጵያ ቤተመዛግብትና ቤተመጽሐፍት አገልግሎት (ወመዘክር) አስታወቀ፡፡

በአሁኑ ወቅት ከ35 በላይ ተቋማት ሰነዶቻቸው በሕጋዊ መንገድ እንዲወገድላቸው ለአገልግሎቱ ጥያቄ ማቅረባቸው ተገልጿል።

የኢትዮጵያ ቤተመዛግብትና ቤተመጽሐፍት አገልግሎት የተቋማትን ሰነዶች የማስወገድ ሥራ መጀመሩን አስታውቋል፡፡ በትናንትናው እለትም የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤትንና የሙገር ሲሚንቶ ሰነዶችን በሕጋዊ መንገድ አስወግዷል፡፡

የአገልግሎቱ ዋና ዳሬክተር ይኩኖአምላክ መዝገቡ በወቅቱ እንደገለጹት፤ ተቋሙ በአዋጅ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት በተቋማት የሚገኙ የተለያዩ ሰነዶችን ለይቶ ያስወግዳል፡፡

በሀገሪቱ ሰነዶችን የማስወገድ ሥራ የተሰጠው ለተቋማቸው ብቻ መሆኑን የገለጹት ዳይሬክተሩ፤ ነገር ግን አንዳንድ ተቋማት ሕገወጥ በሆነ መልኩ ሰነዶችን በእራሳቸው አሊያም በጨረታ በማቅረብ እያስወገዱ መሆኑን አንስተዋል።

ተቋሙ እነዚህ ተቋማትን የማስተማር ሥራ እየሠራ መሆኑን ጠቁመው፤ ችግሩን ለማስተካከል ፍቃደኛ ያልሆኑ ተቋማት በሕግ አግባብ እንደሚጠየቁ አመላክተዋል።

ኢትዮጵያ ለታሪክና ለነባር መረጃዎች ልዩ ትኩረት የምትሰጥ ሀገር ነች ያሉት ዳይሬክተሩ፤ በየጊዜው የሚዘጋጁ ሰነዶች አገልግሎት ባይሰጡም እንኳን ለመዛግብትነት እንደሚቀመጡ ተናግረዋል፡፡

ይወገዱልን ተብለው ወደተቋሙ የሚመጡ ሰነዶች በባለሙያዎች አማካኝነት ምስጢራዊነታቸው ተጠብቆ አይጠቅሙም ተብለው የሚለዩትን እንዲወገዱ በሌላ በኩል ለጥናትና ምርምር እንዲሁም ለታሪክ ይጠቅማሉ ተብለው የሚገመቱ ሰነዶች ደግሞ



ወደ መዛግብት ክፍል እንዲገቡ እንደሚደረግ ገልጸዋል፡፡

ከዚህ በፊት ተቋሙ ሰነዶችን ለማስወገድ ሥልጣን የተሰጠው ቢሆንም ካለው አቅምና የቦታ ውስንነት አንጻር ለበርካታ ጊዜያት ሥራውን ሳያከናውን መቆየቱን አስታውሰው፤ በዚህ ምክንያት በርካታ ተቋማት ጥያቄ እያቀረቡ መሆኑን አንስተዋል፡፡

በአሁኑ ወቅት ተቋሙ ኃላፊነቱን ለመወጣት ተመሳሳይ ሥራ ከሚሠሩ ተቋማት ጋር በመተባበር እንደሚሠራ ገልጸዋል፡፡ የሰነድ አወጋገድ ሂደቱ ዘመናዊ በሆነ መንገድ እንደገና አገልግሎት መስጠት ወደሚችል ጥሬ እቃነት ለመቀየር እንደሚረዳ አስታውቀዋል።

የኢትዮጵያ ቤተ መዛግብትና ቤተመጽሐፍት አገልግሎት የሥልጠናና ማማከር ሥራ አስፈጻሚ እንዲሁም የሰነድ ማስወገድ ኮሚቴ ሰብሳቢ መኮንን ከፋለ በበኩላቸው፤ ሰነዶች በበዙ ቁጥር ሰፊ ቦታና የሰው ኃይል ስለሚጠይቁ አላስፈላጊ ሰነዶችን በማስወገድ ከአገልግሎቱ ጋር በጋራ መሥራት እንዳለባቸው አመላክተዋል፤

በሰነዶች አወጋገድ ዙሪያ በግላቸው እንዲሁም ጨረታ አውጥተው የሚያስወግዱ ተቋማቶች መኖራቸውን ጠቁመው፤ ተቋሙም ይህንን የማስተማርና የማስቆም ሥራ እየሠራ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ከ35 በላይ የሚሆኑ ተቋማት ሰነዶቻቸው በሕጋዊ መንገድ እንዲወገድላቸው መጠየቃቸውን ተናግረው፤ የተለያዩ የግልና የመንግሥት ተቋማት እንደሚገኙበት አስረድተዋል።

# ኢትዮጵያ

## ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ድንጋጌዎችን የሕጓ አካል አድርጋ እየተጠቀመች ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ የሆኑ የሰብዓዊ መብት ድንጋጌዎችን የሕጓ አካል አድርጋ ጥቅም ላይ ማዋሏን የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ አስታወቀ።

በሩስያ ሴንትፒትስበርግ ከሰኔ 19-21 ቀን 2016 ዓ.ም እየተካሄደ በሚገኘው የመብቶች ጥበቃና ሕገ መንግሥታዊ ክትትል /Protection of Rights and Constitutional Supervision/ ዓለምአቀፍ ውይይት ላይ ኢትዮጵያ ተካፍላለች። በመድረኩ ኢትዮጵያን በመወከል የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንትና የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ሰብሳቢ አቶ ቴዎድሮስ ምሕረት የሀገራቸውን ተሞክሮ አቅርበዋል።

አቶ ቴዎድሮስ የሀገራቸውን ተሞክሮ ሲያቀርቡ በኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት የሰብዓዊ መብትና ነፃነት ድንጋጌዎች በስፋት እንደተቀመጡና ዓለምአቀፍ የሆኑ የሰብዓዊ መብት ድንጋጌዎችንም የሕጓ አካል እንዲሆኑ ማድረጓን ጠቁመዋል፡፡

እነዚህን ሕገ መንግሥታዊ መብቶች ለመተርጎም በኢትዮጵያ ያለው አደረጃጀት ለየት ያለ እንደሆነና ሕገ መንግሥትን የመተርጎም ሥልጣን የተሰጠው ለፌዴሬሽን ምክር ቤት እንደሆነ አስረድተዋል፡፡

አክለውም የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔን አደረጃጀት፣ አሠራርና ተግባሩን በመጠቆም ጉባዔው በሕገ መንግሥት ትርጉም ረገድ ያለውን ሚና በስፋት አብራርተዋል፡፡

ጉባዔው ጠንከር ያሉ ሕገ መንግሥታዊ ጉዳዮችን በመመርመር የውሳኔ ሀሳቡን ለፌዴሬሽን ምክር ቤት የሚልክ መሆኑን አንስተዋል።

የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ በኮቪድ 19 ወረርሽኝ ወቅት የዜጎች ሕይወት አደጋ ላይ በወደቀበትና የመንግሥት የሥልጣን ጊዜ ባለቀበት ወቅት ሕገ መንግሥቱን በመመርመር አጣጥሞ በመተርጎም መፍታት መቻሉን ጠቅሰዋል፡

በተጨማሪም አቶ ቴዎድሮስ ምሕረት ከሩስያው አቻቸው ከሚስተር ቫርሊ ዞርኪን ጋር ተገናኝተው በኢትዮጵያና በሩስያ መካከል ያለው ትብብር ተጠናክሮ በሚቀጥልበት ሁኔታ ላይ የሁለትዮሽ ምክክር አድርገዋል፡፡

የሁለትዮሽ ምክክሩ ከኢንዶኔዥያ፣ ከሕንድ፣ ከታይላንድና ከማሌዥያ ሕገ መንግሥታዊ ፍርድ ቤቶች ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንቶችም ጋር በተመሳሳይ ማደረጉን የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ መረጃ ያመለክታል፡፡

በሩስያ ፌዴሬሽን ሕገ መንግሥታዊ ፍርድ ቤት ጋባዥነት በተዘጋጀው ውይይት አቶ ቴዎድሮስን ጨምሮ ከ25 የዓለም ሀገራት የተውጣጡ የሕገ መንግሥታዊ ፍርድ ቤቶች ፕሬዚዳንቶች ተካፍለዋል።

# የቴክኒክና ሙያ

## ሳምንት መዘጋጀቱ ዘርፉ የደረሰበትን ደረጃ ለኅብረተሰቡ ለማሳየት ዕድል ፈጥሯል

**አማን ረሺድ**

<u>አዲስ አበባ፡-</u> የቴክኒክና ሙያ ሳምንት መዘጋጀቱ ዘርፉ የደረሰበትን ደረጃ ለኅብረተሰቡ ለማሳየት ትልቅ ዕድል የፈጠረ መሆኑን በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሥራና ክህሎት ቢሮ አስታወቀ፡፡

በአዲስ አበባ ኤግዚቢሽን ማዕከል ሲካሄድ የቆየው 14ኛው ከተማ አቀፍ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሳምንት የማጠቃለያ መርሐ ግብር በትናትናው ዕለት ተካሂዷል፡፡

በማጠቃለያ መርሐ ግብሩ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሥራና ክህሎት ቢሮ ኃላፊ ደረጃ የኢንተርፕራይዝና ቴክኖሎጂ ልማት ዘርፍ ኃላፊ አቶ መክብብ ወልደሃና እንደገለጹት፤ ሳምንቱ መዘጋጀት ዘርፉ የደረሰበት የቴክኖሎጂና የፈጠራ ደረጃ ለኅብረተሰቡ ለማስገንዘብና የቴክኒክና ሙያ ተቋማትን ትስስር ለማጠናከር ያስቻለ ነው። በዚህም የሙያ ባለቤት የሆኑ ወጣቶች የኅብረተሰቡን ችግሮች ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ለመፍታት ተነሳሽነት እንዲፈጠሩ አስችሏል፡፡

እንደ አቶ መክብብ ገለጻ፤ ቴክኒክና ሙያ ዘርፍ ተወዳዳሪና የሠለጠነ የሰው ኃይል ለማፍራት በልዩ ትኩረት እየሠራ ይገኛል፡፡ በሳምንቱ የቀረቡ የፈጠራ ውጤቶች ተባዝተው የኅብረተሰቡን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚያግዙና ተኪ ምርቶችን በስፋት ለማምረት ተነሳሽነትን የሚፈጥሩ ናቸው፡፡

የቴክኒክና ሙያ ተቋማትን ተደራሽ ለማድረግም በትኩረት ይሠራል ብለዋል።

የቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች ብቁና ተወዳዳሪ የሰው ኃይል በመፍጠር የበኩላቸውን ሚና እንዲወጡ በቀጣይ የአቅም ግንባታ ሥራ እንደሚሠራ አመላክተዋል፡፡

ቴክኒክና ሙያዎች ምርታማነትን በማሳደግ በሚፈለገው ጥራት እና ብዛት፣ ተኪ እንዲሆኑና ችግር እንዲፈቱ ማድረግ እንደሚገባ ጠቅሰው፤ ምርቶቹ መሬት ላይ ካለው ችግር ጋር በማያያዝ ውጤት እንዲያመጡ ቢሮው በቁርጠኝነት እንደሚሠራ ጠቁመዋል፡፡ የገበያ ትስስር መፍጠር እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል፡፡

በሳምንቱ የቴክኖሎጂ ፈጠራ፣ የዕደ ጥበብና የፋሽን ሾው ውድድሮችን ጨምሮ የተለያዩ ሁነቶች የተካሄዱ ሲሆን በከተማው የሚገኙ የቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የሥራ ፈጠራ ባለቤቶች ወጣቶች ምርትና አገር በቀል ሥራዎች ለእይታ ሲቀርቡ ቆይተዋል።

ከሰኔ 15 እስከ 20 ሲካሄድ የቆየው የቴክኒክና ሙያ ሳምንት ከ50 ሺህ በላይ በሚሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች ተጎብኝቷል።

በመርሐ ግብሩ በተለያዩ ዘርፎች ተወዳድረው ያሸነፉ ባለሙያዎችና ኮሌጆች የዋንጫና የተለያዩ የማበረታቻ ሽልማት ተበርክቶላቸዋል።

14ኛው ከተማ አቀፍ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ሳምንት በከንቲባ አዳነች አቤቤ መከፈቱ የሚታወስ ሲሆን በማጠቃለያ መርሐ ግብሩ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሥራና ክህሎት ቢሮ ኃላፊዎች፣ ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ተገኝተዋል።




# ኢንስቲትዩቱ ምርቱን ወደ አንድ ቢሊዮን ዶዝ የሚያሳድግ ቤተ ሙከራ ሊገነባ ነው

**ዘላለም ግዛው**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- ብሔራዊ የእንስሳት ጤና ጥበቃ ኢንስቲትዩት ምርቱን ወደ አንድ ቢሊዮን ዶዝ የሚያሳድግ ቤተ ሙከራ ሊገነባ መሆኑን ገለጸ፡፡ ኢንስቲትዩት የፊታችን ቅዳሜ 60ኛ ዓመት የምሥረታ በዓሉን ያከብራል።

ብሔራዊ የእንስሳት ጤና ጥበቃ ኢንስቲትዩት 60ኛ ዓመት የምሥረታ በዓሉን ምክንያት በማድረግ የኢንስቲትዩቱ የሥራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢና የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ሰብሳቢ አቶ ሃብታሙ ኃይለሚካኤል፣ የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር ታከለ አባይነህ (ዶ/ር)፣ ምክትል ዳይሬክተር በሬቻ ባይሳ (ዶ/ር) እና የሽያጭ ዳይሬክተሩ አቶ መስፍን ታደሰ በጋራ መግለጫ ሰጥተዋል፡፡

አዲስ የሚገነባው ቤተሙከራ ግንባታውን አጠናቅቆ ወደ ምርት ሲሸጋገር አሁን እየተመረተ ያለውን የምርት መጠን በሦስት እጥፍ በማሳደግ ወደ አንድ ቢሊዮን ዶዝ እንደሚያሳድገው ጠቁመዋል፡፡

ወደ ተግባር ለመሸጋገር የአዋጭነት ጥናት እየተከናወነ እንደሚገኝ፣ ዓለም አቀፍ ጨረታ መውጣቱንም ታከለ አባይነህ (ዶ/ር) በመግለጫው አመልክተዋል፡፡

የምርቶቹን መጠን ወደ አንድ ቢሊዮን ዶዝ ማሳደግ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ፈዋሽነታቸው የተረጋገጠ መድኃኒቶችን ማቅረብን ትኩረት ተደርጎ እየተሠራ እንደሚገኝም አመልክተዋል፡፡ ምርቶቹን ለአፍሪካ ሀገራት በመላክም የውጭ ምንዛሪ እጥረትን ለመሸፈን ጥረት ማድረጉም ተገልጿል፡፡

በተለይ እንደፍየል ያሉ ትናንሽ አመንዣኪ እንስሳት የሚያጠቁ ድንበር ዘለል የእንስሳት በሽታዎች እንዲሁም ምርቶቹን አመሳስሎ ለገበያ ማቅረብም ፈተና እንደሆነበትም አመራሮቹ ገልጸዋል፡፡

አቶ መስፍን በበኩላቸው፤ ግብርናው መሠረት ያደረገው የእንስሳት ሃብት ላይ በመሆኑ ምርታማነትን ከማሳደግ አንጻር ከፍተኛ አስተዋፅዖ ማበርከቱን አመልክተዋል፡፡

ሀገራዊ ብልጽግናን ለማሳካት በሚደረገው ሂደትም የኢንስቲትዩቱ አስተዋፅዖ ጉልህ መሆኑን እንዲሁም ያለፉ አፈጻጸሞቹን በመዘከር፣ አሁናዊ አቅሙን በመፈተሽ ለቀጣይ ጊዜ እመርታ ሊሆን በሚችል መልኩ የምንጠቀምበት ይሆናል ብለዋል፡፡

ተቋሙን ሪፎርም በማድረግ የአመራር ለውጥ መደረጉን ያመለከቱት አቶ መስፍን፤ የአሠራር ማሻሻያ ማድረጉን አመልክተዋል፡፡

ለሀገር ኢኮኖሚ አስተዋፅዖ እንዲያደርግ ትኩረት የተሰጠው መሆኑን፣ ከተረጂነት ለመላቀቅ በሚደረገው ጥረትም ትልቅ ተስፋ የተጣለበት ተቋም መሆኑን እና ትርፋማ ሆኖም የአገር ኢኮኖሚን እየደገፈ እንደሚገኝም ነው አቶ መስፍን የጠቆሙት፡፡

በአራት አይነት የእንስሳት ክትባት ምርት የጀመረው ኢንስቲትዩቱ አሁን 23 አይነት የእንስሳት ክትባቶችን በማምረት ላይ እንደሚገኝ ዋና ዳይሬክተሩ ታከለ (ዶ/ር) ተናግረዋል።

በፈረንሳይ ባለሙያዎች ቴክኒካል ድጋፍ እና በ40 ባለሙያዎች ሥራውን የጀመረው ኢንስቲትዩቱ አሁን የቴክኒካል እውቀት ያላቸው 350 የሀገር ውስጥ ባለሙያዎችን መያዙን ነው የገለጹት፡፡

በሰው ኃይል ይመረት የነበረውን ያመራረት ዘዴ በማዘመን በትላልቅ ማሽነሪዎች እያመረተ እንደሚገኝም ጠቁመዋል፡፡

አራት ሚሊዮን ዶዝ ከማምረት ተነስቶ 300 ሚሊዮን ዶዝ ክትባት የማምረት አቅም ላይ መድረሱም ተጠቅሷል።

የሀገር ውስጥ ፍላጎትን በማሟላት ምርቶቹን ወደተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት በመላክ የውጭ ምንዛሪ እያስገባ እንደሚገኝም የሽያጭ ዳይሬክተሩ አቶ መስፍን ገልጸዋል፡፡

ከፍተኛ የእንስሳት እልቂትን ያስከተለውና በዋነኝነት የዳልጋ ከብትን የሚያጠቃው የደስታ በሽታን ከኢትዮጵያ ብሎም ከአፍሪካ ለማጥፋት የተካሄደ ዘመቻን መሠረት አድርጎ የተቋቋመው የከብት ኢንስቲትዩት በሚል በ1956 ዓ.ም የተመሠረተ መሆኑ ይታወቃል።

# ባለፉት 11 ወራት ለዓባይ ግድብ ከአንድ ቢሊዮን 320 ሚሊዮን ብር በላይ ተሰበሰበ

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

<u>አዲስ አበባ፡-</u> በበጀት ዓመቱ ባለፉት 11 ወራት ለዓባይ ግድብ ግንባታ ከአንድ ቢሊዮን 320 ሚሊዮን ብር በላይ መሰብሰብ መቻሉን የታላቁ ህዳሴ ግድብ ማስተባበሪያ ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤት አስታወቀ፡፡ ለግድቡ ግንባታ የመሠረት ድንጋይ ከተቀመጠበት ጊዜ አንስቶ እስከ ግንቦት 30 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ 19 ቢሊዮን 551 ሚሊዮን 206 ሺህ 518 ብር ተሰብስቧል፡፡

የታላቁ ህዳሴ ግድብ ማስተባበሪያ ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤት ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በላከው መግለጫ እንዳስታወቀው፤ በበጀት ዓመቱ ከሐምሌ 1 ቀን 2015 ዓ.ም እስከ ግንቦት 30 ቀን 2016 ዓ.ም ከኅብረተሰብ ተሳትፎ አንድ ቢሊዮን 320 ሚሊየን 870 ሺህ 918 ብር መሰብሰብ ተችሏል፡፡

በበጀት ዓመቱ ሁለት ቢሊዮን ብር ለመሰብሰብ ታቅዶ ባለፉት 11 ወራት አንድ ቢሊየን 320 ሚሊዮን 870 ሺህ 918 ብር በመሰብሰብ የእቅዱን 66 በመቶ ማሳካት መቻሉን ጽሕፈት ቤቱ የላከው መግለጫ ያሳያል፡፡

የተሰበሰበው ገንዘብ ከባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸርም የ10 በመቶ ብልጫ እንዳለው ተገልጿል፡፡

ባለፈው ግንቦት ወር ከኅብረተሰብ ተሳትፎ 106 ሚሊዮን 985 ሺህ 373 ብር መሰብሰቡን የጠቆመው መግለጫው፤ የተሰበሰበው ብር ከባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር የ10 ነጥብ አራት በመቶ



ቅናሽ ማሳየቱን አስታውቋል፡፡

ከኅብረተሰብ ተሳትፎ የተሰበሰበው ብር ከሀገር ውስጥ ቦንድ ስጦታ፣ ከዲያስፖራ ቦንድ ስጦታ፣ ከፒን ሽያጭ ገቢ፣ በ8100 አጭር የጽሑፍ መልዕክት እንዲሁም በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል የስጦታ አካውንት መሆኑን ጊዜያዊ ማስተባበሪያ ፕሮጀክት ጽሕፈት ቤቱ በላከው መግለጫ አመላክቷል፡፡

የግድቡ ግንባታ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ አጠቃላይ ከተሰበሰበው 19 ቢሊዮን 551 ሚሊዮን 206 ሺህ 518 ብር ውስጥ 17 ቢሊየን 115 ሚሊዮን 836 ሺህ 526 ብር በመሰብሰብ የሀገር ውስጥ ቦንድ ሽያጭ ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ሀገርን የዳቦ ቅርጫት የማድረግ የቀደመ ራዕይ ስኬት ጅማሮ !

ሀገራችን በብዙ የተፈጥሮ ሀብቶች የታደለች ብትሆንም እነዚህን ሀብቶች ወደሚጨበጥ ልማት መለወጥ ባለመቻሏ የድህነት እና የኋላ ቀርነት መገለጫ በመሆን ረጅም ዓመታትን አሳልፋለች። በየጊዜው ከሚያጋጥሟት ችግሮች ለመውጣትም እጆቿን ዘርግታ የሌሎችን ምፅዋት ስትጠብቅም ኖራለች።

ይህንን ሀገራዊ ችግር ለመሻገር በየዘመኑ የነበሩ ትውልዶች የተለያዩ ጥረቶችን ቢያደርጉም፣ በዘመናት ከሚከተለን የግጭት አዙሪት መውጣት ባለመቻላችን፣ ጥረቶቹ ውጤት አምጥተው የምንመኛትን ያደገች፣ የበለፀገች፣ ለዜጎቿ የተመቸች፣ የትምክህት ምንጭ የሆነች ሀገር ለመፍጠር ሳንችል ቀርተናል።

ባለፉት ስድስት አስርተ ዓመታት ያሉትን ሀገራዊ ትርክቶች እንኳን ብንመለከት፣ በነዚህ ዓመታት ውስጥ እንደ ሀገር የጀመርናቸው የለውጥ ንቅናቄዎች ዋነኛ ዓላማ ሀገርን ከድህነት እና ከኋላ ቀርነት የመታደግ፣ ሀገራዊ የማደግ፣ የመበልፀግ መሻትን እውን ለማድረግ ከፍ ባለ መነቃቃት የተጀመሩ ናቸው።

በተለይም እንደ ሀገር በምግብ እህል ራስን ለመቻል የሚደረጉ ጥረቶች በየዘመኑ ከፍ ያለ ትኩረት ተሰጥቷቸው ተግባራዊ ሆነዋል። የ66 ለውጥ ሀገር ከፍተኛ በሆነ የድርቅ አደጋ የተመታችበት፣ በሺዎች የሚቆጠሩ ለሞት የተዳረጉበት ከመሆኑ ጋር በተያያዘ "ኢትዮጵያን የዳቦ ቅርጫት እናደርጋለን" የሚል መፈክር የተስተጋባበት እንደነበር የሚታወስ ነው።

በርግጥም ሀገሪቱ ካላት ከፍተኛ የውሀ ሀብት፣ ለእርሻ ተስማሚ አየር፣ የሚታረስ መሬት እና ሰፊና የሚተጋ የሰው ጉልበት አንጻር፣ "ኢትዮጵያን የዳቦ ቅርጫት እናደርጋለን" የሚለው የዘመኑ ትውልድ መነቃቃት፣ ወደ ተግባር ተለውጦ ተጨባጭ ፍሬ የማያፈራበት ምንም ተጠየቅ አልነበረውም። መነቃቃቱም እንደተባለው ሀገሪቱን የዳቦ ቅርጫት ለማድረግ የነበረው አቅም ከፍያለ ነበር።

ይህም ሆኖ ግን ለውጡና ለውጡ የተገዛበት ሀገራዊ መንፈስ በተለያዩ ቡድናዊ ፍላጎቶች እየተቀዛቀዘ፣ ፍላጎቶች የሚስተናገዱበት የፖለቲካ አስተሳሰብ እና አስተሳሰቡን የሚሸከም ሀገራዊ አእምሮ መፍጠር ባለመቻላችን ነገሮች ወዳልታሰበ አቅጣጫ ሄደው፣ ሀገር እና ሕዝብ ያልተገባ ዋጋ ለመክፈል የተገደዱበት ታሪካዊ ክስተት ተፈጥሯል።

በዘመነ ደርግ ሀገርን የዳቦ ቅርጫት የማድረጉ መነሳሳትን ተጨባጭ ለማድረግ የተለያዩ ጥረቶች ተደርገዋል። አረንጓዴ የምርት ዘመቻ በሚል ሀገራዊ አቅሞችን በማቀናጀት ምርት እና ምርታማነትን ለማሳደግ ረጅም ርቀት መጓዝ ተችሏል፣ ዘመናዊ የመንግሥት እርሻዎችን በማስፋፋት ሀገራዊ ችግሩን ለመሻገር የተደረገው ጥረትም የዚሁ እውነታ አካል ነበር።

ጥረቱ በመንግሥት እና በተለያዩ ቡድኖች መካከል በነበሩ የተቃርኖ ፍላጎቶች እና፣ ፍላጎቶቹን በኃይል ተግባራዊ ለማድረግ በተፈጠሩ አውዳሚ የእርስ በርስ ግጭቶች/ጦርነቶች የተነሳ የተጠበቀውን ያህል ውጤት ሳይሆን ቀርቷል። ያም ሆኖ ግን ጥረቱ እንደ ሀገር ያሉንን አቅሞች አቀናጅተን መንቀሳቀስ ከቻልን ስኬታማ መሆን እንደምንችል ተጨባጭ ማሳያ መሆን ችሏል ።

በዘመነ ኢሕአዴግ የተሻለ ሀገራዊ ሠላም ቢኖርም፣ ኢሕአዴግ መራሽ መንግሥት እንደ ሀገር ግብርና መር ኢኮኖሚ ተግባራዊ እንደሚያደርግ በፖሊሲ ደረጃ ቢያስቀምጥም፣ ከፖሊሲ አቅጣጫ ባለፈ ለዘርፉ ተገቢውን ስትራቴጂክ ትኩረት ባለመስጠቱ እንደ ሀገር በምግብ እህል ራስን የመቻል የስድስት አስርተ ዓመታት ጉዟችን ትርጉም ያለው ውጤት ማምጣት ሳይችል ቀርቷል።

ከለውጡ ማግስት በሕዝብ አዎንታ ወደ ሥልጣን የመጣው ብልፅግና መንግሥትም ቢሆን ይህን በትውልዶች መካካል ከፍ ያለ ራዕይ ሆኖ የቆየውን በምግብ እህል ራስን የመቻል፣ ከዚያም አልፎ ለሌሎች የመትረፍ ሀገራዊ መሻት ተጨባጭ እውነታ ለማድረግ ሰፊ ጥረቶችን እያደረገ ይገኛል። እየተመዘገበ ያለውም ውጤት ተስፋ ሰጭ መሆኑ የአደባባይ ሚስጥር ነው።

የለውጥ ኃይሉ በምግብ እህል ራስን ለመቻል ከዚያም አልፎ በልማት ድህነትን ታሪክ ለማድረግ የጀመረው ሀገራዊ ጥረት፣ በሕዝብ ውስጥ አዲስ መነቃቃት በመፍጠር፣ ትርጉም ያለው ተጨባጭ ውጤት እያስመዘገበ ነው። ለዚህም በበጋ የስንዴ መስኖ ልማት፣ በሌማት ትሩፋት ወዘተ እየተመዘገበ ያለው ስኬት ተጠቃሽ ነው።

ይህ አሁናዊ የጅማሮ ስኬት አጠቃላይ ለሆነው ድህነትን ታሪክ የማድረግ ሀገራዊ ጉዞ ሆነ፣ በምግብ እህል ራስን ለመቻል ለሚደረገው ጥረት ትልቅ ሀገራዊ መነቃቃት እየፈጠረ ነው። ሀገሪቱ ካላት ከፍተኛ የውሀ ሀብት፣ ለእርሻ ተስማሚ አየር፣ የሚታረስ መሬት እና ሰፊ የሰው ጉልበት አንጻር፣ "ኢትዮጵያን የዳቦ ቅርጫት እናደርጋለን" የሚለው የቀደመው ዘመን ትውልድ መነቃቃት፣ ወደ ተግባር ተለውጦ ተጨባጭ ፍሬ ማፍራት እንደሚችልም እያመላከተ ነው።

አሁን ላይ ተስፋ ሰጭ የሆነው ሀገርን የዳቦ ቅርጫት የማድረግ የትውልድ መሻት፣ በምግብ እህል ለራሳችን በቅተን ለሌሎች የምንተርፍ ራዕይ በዚህ ትውልድ ተፈጻሚ እንዲሆን፤ ዛሬ ላይ ከትናንት ስህተቶቻችን ቆም ብለን መማር፤ የትናንቱ ትውልድ ይህን መሻቱን ለምን ተጨባጭ ማድረግ አቃተው ብለን መጠየቅ ይኖርብናል። እንደ ትውልድ የሚጠበቅብን ተወጥተን እንድናልፍ ያለን ተስፋም ይኼው ነው።

ለዚህ ደግሞ ከሁሉም በላይ በየዘመኑ የነበሩ ትውልድ ስለሀገራቸው ያለሟቸው ትላልቅ ሕልሞች እውን እንዳይሆኑ ፈተና ለሆነው የፖለቲካ ባሕላችን ተገቢውን ትኩረት ሰጥተን፤ እንደ ሀገር በሰከነ መንፈስ እና በጠራ አእምሮ ልንቀሳቀስ ይገባል። ይህን ማድረግ ባለመቻላችን ሊፈጠር ለሚችለው የሕልም መጨናገፍ ትውልዱ የታሪክ ተጠያቂ መሆኑ የማይቀር ነው!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው።በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

## አረንጓዴ ዐሻራ - ለሁለንተናዊ ልማት

በግርማ ሞገስ

የበለፀጉ ሀገራት አሳሳቢ የሆነውን የአየር ንብረት ለውጥ ለመግታት የአረንጓዴ ኢኮኖሚና መሰል ስምምነቶች እንዲሁም ፖሊሲዎችን ነድፈን እየሠራን ነው ይላሉ፤ ይሁንና በተግባር ሲታይ መሬት ላይ ጠብ ያለ ነገር አይስተዋልም። እነዚህ የበለፀጉ ሀገራት የሚለቅቁት በካይ ጋዝ በማደግ ላይ የሚገኙ እንደ አፍሪካ ያሉ ሀገራትን እያሳሰበ ነው። በመሆኑም ይህን ለመቀነስ "ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ኢኮኖሚ እና መሰል ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን ለመተግበር እየተንቀሳቀሱ ነው።

የጥንቱ የኢትዮጵያ ምድር 120 ሚሊዮን ሄክታር ማለትም 60 በመቶው በደን የተሸፈነ እንደነበር የታሪክ ድርሳናት ያስረዳሉ። ዲያቆን ተረፈ ወርቁ፣ "አረንጓዴ አሻራ ከዓጤ ምኒልክ እስከ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)" በተሰኘ ጽሑፋቸው እንደተየቡት ከሆነ፤ ዓፄ ምኒልክ ስለደን ሀብት ጠቃሚነት ‹‹የንጉሥ የደን ክልል›› በሚል እሳቤ አፅንዖት በመስጠት በንግሥና ዘመናቸው የመጀመሪያውን የደን ሥርዓት መሥርተው ነበር። የደን ሕግ ለማርቀቅም የውጭ አገር ባለሙያዎችን ቀጥረው ያሠሩ እንደነበር ጽሑፉ ያብራራል።

ኢትዮጵያን በደን ለማልማት ካላቸው ቀና አመለካከት የተነሣም በፍጥነት የሚያድጉ ዛፎችን ከሌሎች አገራት ያስመጡ የነበር ሲሆን፣ ሕዝቡ የተፈጥሮ የደን ሀብትን እንዲንከባከብ ያበረታቱ እንደነበር ስለንጉሡ የተጻፉ ታሪኮች ያስረዳሉ። ንጉሡ፣ የደን አጠባበቅን በተመለከተ ያወጡት ሕግ ደንን አላግባብ የሚጨፈጭፉ ሰዎች ንብረታቸውን በመውረስና እስከ ሞትም በሚያደርስ የቅጣት ርምጃ ይወሰድባቸው ነበር። ከዓፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ ኢትዮጵያን የመሩ መንግሥታትም በየዘመናቸው እንደየድርሻቸው የደን ሀብትን ለመጠበቅ ሠርተዋል።

ከ15 ዓመታት በፊት ኢትዮጵያ "ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ኢኮኖሚ" ስትራቴጂን ቀርፃ መንቀሳቀስ የጀመረችው በአቶ መለስ ዜናዊ አማካኝነት ነው፣ በዘርፉ የበርካታ አገሮችን ትኩረት መሳብ ችላለች። እንደ አሜሪካ ያሉ የበለፀጉ ሀገራት ኢትዮጵያ እየተገበረችው ላለው የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ስትራቴጂ ድጋፋቸውን እየሰጡ እንደሚገኙ መረጃዎች ያሳያሉ።

ኢትዮጵያ ሀገራችን የነደፈችውን የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ስትራቴጂ ተከትላ በሀገር ውስጥ የምታከናውናቸው ሥራዎች የራሷን ልማትና ዕድገት የሚያፋጥኑ፣ ለዓለም ሥጋት የሆነውን የአየር ንብረት ለውጥ ለመከላከልና አደጋዎቹን ለመቀነስ ትልቅ አስተዋፅዖ እንደሚኖረው ውሎ ያደረ ሐቅ ነው።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ወደ መንበረ ሥልጣናቸው ከመጡ ወዲህ የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር በትኩረት እየተሠራ ይገኛል። አረንጓዴ ኢኮኖሚን፣ የአካባቢ ጥበቃንና የተፈጥሮ ሀብት መንከባከብን ትኩረት ያደረገ ነው። የተፈጥሮ ሀብትም ሆነ የዕፅዋቶችና የደኖች መመናመን ጉዳይ በኢትዮጵያ ላይ እያደረሰ ያለው ጥፋትና ቀውስ ከፍተኛ መሆኑ ከግምት ውስጥ በመውሰድ መላው ሕዝብ ከጎናቸው በማሰለፍ የአረንጓዴ ዐሻራ ልማት ሌጋሲን እያስቀጠሉ ነው።

ባለፈው ዓመት ‹‹በአረንጓዴ ዐሻራ›› ዘመቻ በሀገሪቱ ሁሉም ክልሎች በተደረገው የችግኝ ተከላ በዓለም አቀፍ ደረጃ ሳይቀር ትልቅ ትኩረትን የሳበ ነበር። ይህ መርሐግብር ኢትዮጵያን በአፍሪካና በዓለም አቀፍ መድረክ የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ልማት ሞዴል የማድረግ እንቅስቃሴው የበርካታዎችን ይሁንታንና ድጋፍን እያገኘ መሆኑንም በስፋት እያስተዋልን ነው። ይህን ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ያለው የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር ሀገር በሁሉም ዘርፍ እንድትለማ ማድረግ የሁሉም ዜጋ ኃላፊነት ቢሆንም በግንባር ቀደምትነት የአመራሩ ድርሻ ይጠቀሳል።

"ስለደን ጥቅም እውቁ" የሥነጽሑፍ ሰው ፈቃደ አዘዘ (ዶ/ር) (1994 ዓ.ም. ጀርመን/ሀምቡርግ) በሚል የግጥም መድብላቸው፤

**አንድ ዛፍ ቆርጣችሁ፣**
**ሁለት ካልተካችሁ፣**
**የተፈጥሮ ጠላት፣**
**የደን አሸባሪ፣**
**የሰው ልጅ አዋኪ፣**
**የተፈጥሮ ፀሯ- ነፍሰ ገዳይ** ናችሁ። በማለት የሰው ልጅ ስለዛፍ ጥቅም እንዲገነዘብ ለማድረግ ሞክረዋል።

**ኢትዮጵያ የያዘችው የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ስትራቴጂ የአየር ንብረት ለውጥን መቋቋምና ዝቅተኛ የካርበን ልቀት መጠን እንዲኖር የሚያደርግ ግብ ነው**

ኢትዮጵያ የያዘችው የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ስትራቴጂ የአየር ንብረት ለውጥን መቋቋምና ዝቅተኛ የካርበን ልቀት መጠን እንዲኖር የሚያደርግ ግብ ነው። ታዲያ ይህ ስትራቴጂ የኢትዮጵያን ልማት እና ዕድገት የሚያቀላጥፍ፤ ዘላቂነቱን አስተማማኝ የሚያደርግ አካባቢ እንደሚፈጥር ጥናቶች ይጠቁማሉ። ተፈጥሮን ከመንከባከብና ተጠቃሚ ከመሆን በተጨማሪ ለብክለትና ለውድመት ከሚዳርጉ አደጋዎች ጠብቆ ለማቆየት ሁነኛ መፍትሔ የያዘ መሆኑ ታምኖበት እየተሠራበት ያለ ሥራ ነው።

የችግኞች ጠቀሜታ በሳይንሳዊ ትርጓሜ የሰው ልጅ የሚተነፍሰውን አየር በመቀበል መልሰው ለትንፈሳ እንደሚለቁት ይተረጉማሉ። ይህ ማለት ጤናማ ትንፈሳ እንዲኖር፣ ሕይወት እንዲቀጥልና እንዲያንሰራራ በማድረግ ኑሮ እንዲቀጥል ያስችላል። የዘርፉ ምሑራንም እንደሚያስረዱትም፤ ችግኞች ወይም ደኖች ለሰው ልጅ ብቻ ሳይሆን ለፍጡራን ብሎም የሰው ልጅ ለሚጠቀምባቸው እንደ ቡና፤ አቮካዶና መሰል የአትክልትና ፍራፍሬዎች ውጤታማ መሆን አስፈላጊ ናቸው።

በኢትዮጵያ አርሶ አደሩ ማኅበረሰብ ‹‹አንድ ልጅ ስትወልድ አንድ ችግኝ ትከል›› የሚል ብሂል አለው። ይህ አባባል ችግኝ መትከል ማለት ልጅን እንደማሳደግ የሚቆጠር ነው። ልጅን ወልዶ ለቁም ነገር እስኪበቃ ወላጅ አስፈላጊውን እንክብካቤ በማድረግ ይተጋል። ችግኞችንም እንደ ልጆች መንከባከብ ሕይወትን ያስቀጥላል። አርሶ አደሮች፣ ዛፍ ሲኖር ዝናብ ሲጥል መጠጊያ እንዲሁም ፀሐይም ሲሆን መጠለያ አለፍ ሲልም ለቁሳቁስ መሥሪያ ስለሚሆኑ እንደሚንከባከቧቸው ይናገራሉ።

ችግኞችን በመትከል መንከባከብ የንጹሕ መጠጥ ውሃ ተጠቃሚ መሆንን ከማረጋገጥ በተጨማሪ ንጹሕ አየር በማግኘቱ ረገድ የማይተካ ሚና የሚጫወቱ መሆናቸውን መዘንጋት አያስፈልግም። በተጨማሪም ወረርሽኝ የሆኑ በሽታዎችን ከመከላከልና በአየር ንብረት ለውጥ ሳቢያ የሚደርሱ ጉዳቶችን በመቀነስ ረገድ ትልቅ አስተዋፅዖ አላቸው። ኢትዮጵያም የዚህን አስፈላጊነት በመረዳት በትኩረት እየሠራች ትገኛለች።

ከዚህ አንጻርም የችግኝ ተከላ መርሐ ግብሩ ከ2011 ዓ.ም እስከ 2014 የተከናወነ ሲሆን፣ በእነዚህ ጊዜያት 25 ቢሊዮን ችግኞች የተተከሉ መሆናቸውን መረጃዎች ያመለክታሉ።

ሀገራችን ኢትዮጵያ አረንጓዴ ውበት ብሎም ጤነኛ ዜጋ ይኖራት ዘንድ ችግኝ መትከል፣ ዕፅዋቶችን መንከባከብ፣ ደኖቻችንን ከጭፍጨፋ መከላከል ከሁሉም ሰው የሚጠበቅ ኃላፊነት ነው። ስለሆነም በተያዘው ክረምት በመጪው ሰኞ የሚጀምረው 500 ሚሊዮን ችግኞች የመትከል መርሐ ግብር ላይ ሁሉም ዜጋ በኃላፊነት ችግኝ በመትከልና የተተከሉትንም በመንከባበከብ ለኢትዮጵያ አረንጓዴ ሕይወትና ውበት የበኩሉን ሊወጣ ይገባል እንላለን።

## ነፃ ሃሳብ

# ለኦዲት ግኝቱ አስተማሪ የእርምት ርምጃ

**ስሜነህ ደስታ**

ባለበጀት መሥሪያ ቤቶች ሰኔ ወር ገብቶ ሳይጠናቀቅ የተለያዩ ግዥዎችን ለመግዛት ፣ የተለያዩ ክፍያዎችን ለመክፈል፣ የዱቤ አገልግሎቶችን ለመሰብሰብ መሯሯጥ የነበረ አሁንም ያልተቀረፈ ተግባር መሆኑ በተለያዩ አጋጣሚዎች ይስተዋላል። ይህ የሚያመላክተው ከሥር ከሥሩ በየጊዜው ነገሮችን ከማከናወን ይልቅ በተለያዩ ምክንያቶች ማጓተት እንዳለ እና ሰኔ ተጠናቆ ኦዲተር ሲመጣ ለኦዲተር ሪፖርት ለማቅረብ እንዲረዳ(እንዲያመች) በሚል ብቻ በእውር ድንብር የሚከናወን ተግባር መሆኑን ነው።

ይህን የእውር ድንብር አካሄድ ተከትለው ቢንቀሳቀሱም ሁሉንም ማሳካት አቅቷቸው እንዳይደርስ ብለው የሚሯሯጡለት ሰኔ 30 እንደይማደርስ የለም ደርሶ ያልፍባቸዋል። ኦዲተር ደግሞ በበጀት ዓመቱ የተፈቀደ ገንዘብ በበጀት ዓመቱ በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን እና በበጀት ዓመቱ ለተሰጠ አገልግሎት በበጀት ዓመቱ መሰብሰቡን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል። እንዲሁም በጉድለት፣ በብክነት፣ ገንዘብ ባለመሰብሰብ፣ ሥራን በተገቢ ሁኔታ ባለመምራት፣ ወዘተ. በማለት በኦዲት አሠራር ሥርዓት መሠረት አጋልጦ ያቀርባል።

በአሠራር ሥርዓቱ መሠረት የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤትም በበጀት ዓመቱ ማጠቃለያ ላይ የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት እና የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያቀርባል። በዚህ ዓመትም ሰሞኑን በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሶስተኛ ዓመት 32ኛ መደበኛ ስብሰባ ላይ የፌዴራል ዋና ኦዲተር የ2015 ዓ.ም. የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት እና የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት አቅርቧል።

ሪፖርቱን ያቀረቡት ዋና ኦዲተር ወይዘሮ መሠረት ዳምጤ፤ በ2014 ዓ.ም. 92 መሥሪያ ቤቶች በኦዲት ግኝት መሠረት ተመላሽ እንዲያደርጉ አስተያየት ከተሰጠበት 443 ሚሊዮን ብር እና 23 ሺህ ዶላር ውስጥ ኦዲት ሲሠራ ተመላሽ የተደረገው ብር 48 ነጥብ 2 ሚሊዮን ብር ብቻ መሆኑን አስታውቀዋል። 394 ነጥብ 8 ሚሊዮን ብር ተመላሽ አልተደረገም ማለት ነው። የዚህ አፈጻጸሙ ሲታይ 11 በመቶ ብቻ ነው። ይህ የሚያመላክተው መሥሪያ ቤቶቹ ተመላሽ እንዲያደርጉ አስተያየት ሲሰጣቸው አስገዳጅ ሁኔታ አለመኖሩን እንዲሁም ተመላሽ እንዲያደርጉ የሚከታተላቸው አካል በአግባቡ የመከታተል ክፍተት እንዳለበት ነው።

በኦዲት ሪፖርቱ በ2015 ዓ.ም በ124 መሥሪያ ቤቶች በጠቅላላው ብር 14 ነጥብ 1 ቢሊዮን በወቅቱ ያልተወራረደ ወይም ያልተሰበሰበ ተሰብሳቢ ሂሳብ መኖሩ ቀርቧል። ለውሎ አበል እና ለመጓጓዣ እንዲሁም ለግዥ የተሰጠ ክፍያ ሠራተኛው ሥራውን አጠናቆ ከተመለሰ በኋላ በ7 ቀናት መወራረድ እንዳለበት መመሪያው ቢያዝም ተቋማቱ ገንዘቡን በወቅቱ ባለማወራረዳቸው ከፍተኛ ውዝፍ ተሰብሳቢ ገንዘብ ይኖርባቸዋል። ይህ ያልተሰበሰበ ወይም ውዝፍ ሂሳብ ከተገኘባቸው ተቋማት መካከል በከፍተኛ መጠን ቀዳሚውን ሥፍራ የሚይዘው ጤና ሚኒስቴር ነው፤ መጠኑም 6 ቢሊዮን ብር ነው። ሌሎች መሥሪያ ቤቶችም በቢሊዮን እና በመቶ ሚሊዮን ብር ደረጃ የተጠቀሰ ገንዘብ ማሰባሰብ አለመቻላቸው በሪፖርቱ ተጠቅሷል።

ከአንድ መሥሪያ ቤት 6 ቢሊዮን ብር እንደቀላል ሳይሰበሰብ የቀረ ተብሎ ይገለጽ እንጂ ይህ ገንዘብ ቢሰበሰብ ለሀገር የሚሰጠው ፋይዳ ከፍተኛ ይሆናል (በአግባቡ ወጪ የሆነም ካለ በወጪ ተይዞም ቢሆን)። ይህ ሁኔታ በአፋጣኝ ለየት ያለ ንቅናቄ ተፈጥሮም ይሁን ወይም በሌላ መንገድ ተመላሽ ገንዘቡ ተሰብስቦ ገቢ መሆን ካልቻለ፤ እንዲሁም ለቀጣይ የሚሰበሰብ ገንዘብ በወቅቱ ተመላሽ እንዲደረግ የሚያስገድድና ከተለመደው አካሄድ በተለየ ጠንከር ያለ አሠራር፣ የቁጥጥር ሥርዓት እንዲሁም የተጠያቂነት አግባብ መከተል ካልተቻለ ዛሬ በሚሊዮን ደረጃ ሳይሰበሰቡ የቀሩ መሥሪያ ቤቶች ነገ ወደ ቢሊዮን ብር ማደጋቸው አይቀሬ ይሆናል።

> **ሌላው የሚገርመው ጉዳይ**
> የኢምግሬሽን እና ዜግነት አገልግሎት ከገንዘብ ሚኒስቴር እውቅና ውጪ ከፓስፖርት አገልግሎት ጠያቂዎች 17 ሚሊዮን ብር በሕገወጥ መንገድ በግለሰብ የባንክ ሂሳብ ቁጥር ሰብስቧል ተብሎ በሪፖርቱ የቀረበ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ 9 ሚሊዮን ብሩን ለሠራተኞች የበዓል ስጦታ እና የትርፍ ሰዓት ክፍያ እንዳዋለው ተገልጿል

ሌላኛው የፌዴራል ዋና ኦዲተር በሪፖርቱ የጠቀሰው ጉዳይ በፌዴራል መንግሥት የሚገነቡ ፕሮጀክቶች ጉዳይ ሲሆን፣ የሥራ ተቋራጮች ከዚህ በፊት የነበራቸው የሥራ አፈጻጸም ሳይታይ በሌሎች የግንባታ ጨረታዎች ላይ እንዲወዳደሩ ተደርጎ ማሸነፋቸው ተገልጾላቸው ግንባታ ጀምረዋል። በዚህም 11 ቢሊዮን ብር ገደማ ዋጋ ያላቸው 12 የግንባታ ፕሮጀክቶች ለሁለት የሥራ ተቋራጮች ተሠጥቷል።

ለዚህ ተጠያቂ የሚሆነው የሥራ አፈጻጸማቸው ሳይታይ እንዲገነቡ የፈቀደላቸው መሥሪያ ቤት ብቻ ሳይሆን መሥሪያ ቤቱን የሚቆጣጠረውም አካል መሆን አለበት። ምናልባት ‹‹እኔ በዚህ ልክ እንደነበረ አላውቅም›› የሚል ከሆነ ከእኛ እኩል መስማት አይገባህም፤ መቆጣጠር ነበረብህ ብለን ድርቅ ሳንል እስቲ በቀጣይ የተወሰደውን የማስተካከያ ርምጃ አሳየን እንላለን። ርምጃ ተወስዶ ማሳየት ካልተቻለ ግን ተቆጣጣሪውም ...።

ይህ ብቻ ሳይሆን የግንባታ ፕሮጀክቶች መቋረጥ መንግሥትን ለሀብት ብክነት እየዳረገው ይገኛል። የፌዴራል ዋና ኦዲተር ሪፖርት እንደሚያሳየው ለናሙና ከታዩ 41 የተቋረጡ ፕሮጀክቶች መንግሥትን 17 ቢሊዮን ብር ተጨማሪ ወጪ እንዲያወጣ እድርጎታል። 17 ቢሊዮን ብር ተጨማሪ ወጪ ከማስወጣቱ በላይም ግንባታዎችን የሚቆጣጠረው የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ባለሥልጣን ግንባታዎች ከተቋረጡ በኋላ የተከፈሉ የቅድመ ክፍያዎችን አላስመለሰም እንዲሁም የመልካም ሥራ አፈጻጸም ዋስትና ገንዘብን ተከታትሎ አላስፈጸመም። ይህን የተከፈለ ቅድመ ክፍያ ባለሥልጣኑ ተከታትሎ ማስመለስ ካልቻለ ታዲያ ማን ተከታትሎ ያስመልስ? ባለሥልጣኑን የሚከታተሉ የሚመለከታቸው አካላት ዋና ኦዲተሩ የሚያቀርባቸውን ሪፖርቶች በትኩረት በማየት አስፈላጊው ርምጃ እንዲወሰድ በከፍተኛ ሁኔታ መትጋት አለባቸው።

ሌላው የሚገርመው ጉዳይ የኢምግሬሽን እና ዜግነት አገልግሎት ከገንዘብ ሚኒስቴር እውቅና ውጪ ከፓስፖርት አገልግሎት ጠያቂዎች 17 ሚሊዮን ብር በሕገወጥ መንገድ በግለሰብ የባንክ ሂሳብ ቁጥር ሰብስቧል ተብሎ በሪፖርቱ የቀረበ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ 9 ሚሊዮን ብሩን ለሠራተኞች የበዓል ስጦታ እና የትርፍ ሰዓት ክፍያ እንዳዋለው ተገልጿል። ከዚህ በተጨማሪም አገልግሎቱ በተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት የፓስፖርት አገልግሎትን በውክልና እንደሚሰጥ የተገለፀ ነገር ሳይኖር ቪዲቸር (viditture) ለተባለ የግል ድርጅት የውል ስምምነት በማድረግ ውክልና የሰጠ መሆኑን የዋና ኦዲተር ሪፖርት ይፋ አድርጓል።

የግል ድርጅቱ ከሀገር ውጭ ያሉ ነዋሪዎች ለፓስፖርት አገልግሎት ኦንላይን ሲያመለክቱ ሰነዱን አጣርቶ፣ ከኢምግሬሽን ፓስፖርቱ ተዘጋጅቶ ሲያልቅ ተቀብሎ ወደ ደንበኛ ለማስተላለፍ ተገልጋዩ ለኢምግሬሽን ከከፈለው በተጨማሪ 100 ዶላር እንደሚያስከፍል ኦዲቱ አጋልጧል። ቪዲቸር የተባለው አስከፋዩ ድርጅት ይህንን ሥራ ለመሥራት የተመረጠበት መስፈርት፣ የግዢ ሂደት እና ፓስፖርትን ለማሠራጨት ፈቃድ ያለው መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃም አላቀረበም። ይሄ ብቻ ሳይሆን የፓስፖርት ሥራ ለመሥራት በሀገሪቱ የንግድ ሕግ መሠረት ንግድ ፈቃድ አላወጣም፤ በታክስ ሕጉ መሠረት ግብር የማይከፍል ነው። ይህ የሚያመላክተው ሥርዓትና ሕግ እየተከበረ አለመሠራቱን ብቻ ሳይሆን በግለሰብ ኃላፊ መልካም ፍቃድ መሥሪያ ቤቶች እየተመሩ መሆኑን ነው። ለዚህም ገደብ ሊበጅለት ይገባል።

በኦዲት ሪፖርቱ በ 14 መሥሪያ ቤቶች 1 ነጥብ 7 ቢሊዮን ብር በተከፋይ ተመዝግቦ የተያዘ መሆኑን፣ ነገር ግን ለማን እንደሚከፈል ተለይቶ የማይታወቅ እንደሆነ፤ 30 የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች 16 ሚሊዮን 470 ሺህ ብር ከደንብና መመሪያ ውጪ አላግባብ መክፈላቸው፤ መሥሪያ ቤቶች በፋይናንስ አስተዳደር አዋጁ መሠረት የተመደበውን በጀት ለታለመለት ዓላማ ማዋል የሚጠበቅባቸው ቢሆንም የገንዘብ ሚኒስቴር ስምንት ቢሊዮን ብር፣ የጤና ሚኒስቴር ሁለት ቢሊዮን ብር፣ ግብርና ሚኒስቴር 1 ነጥብ 2 ቢሊዮን ብር፣ ወዘተ. ከአዋጁ ውጭ ከታለመለት ዓላማ በተለየ ማዋላቸው ቀርቧል። እንደነዚህ አይነት ተግባራት ሲከናወኑ ተከታትሎ የእርምት (የማስተካከያ) እርምጃ የሚወስድ አካል ያስፈልጋቸዋል።

እኛ እንግዲህ አስፈጻሚውን አካል ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ ጉድለት ሲገኝ ማስተካከያ ወይም የእርምት ርምጃ ይወስዳል፤ እንዲሁም እንዲወሰድ ያስደርጋል ብለን በዋነኛነት የምንለው ፓርላማውን ነውና ፓርላማው ለጉዳዩ ተገቢውን ትኩረት ሰጥቶ ሊንቀሳቀስ ይገባል። ይህንን የማድረግ የሞራልም የህግም ሃላፊነት አለበት ።

የእርምት ርምጃዎችን በተመለከተ የገንዘብ ሚኒስቴር በ2014 በጀት ዓመት በቀረበለት ሪፖርት መሠረት ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት ከተሰጠባቸው 19 የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች እና የኦዲት አስተያየት ሊሰጠባቸው ባልቻሉ ስድስት ተቋማት ላይ የተለያዩ ርምጃዎችን መውሰዱ ተገልጿል።

ከነዚህ መካከል በስድስት ዩኒቨርሲቲዎች እና በሰባት የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ላይ የገንዘብ ቅጣት እና ከባድ የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ መጻፉን ዋና ኦዲተሯ አመላክተዋል። በተጨማሪም ሶስት የዩኒቨርሲቲ አመራሮችም ከኃላፊነታቸው እንዲነሱ መደረጉንም አንስተዋል። ጅምሩ ጥሩ ቢሆንም የእርምት ርምጃው በጣም ጥቂት ከመሆኑ በተጨማሪ ብዙ እርቀት መሄድ የሚገባው ነው። ከኃላፊነት ማንሳት ብቻ ሳይሆን በህግ አግባብ ተጠያቂ አድርጎ ውሳኔ ማሰጠትም ይገባል።

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የአሠራርና የአባላት ሥነ ምግባር ደንብ መሠረት፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ የሥነ ምግባርና ፀረ ሙና ኮሚሽን፣ የሠብዓዊ መብቶች ኮሚሽን፣ የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋምና የዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ዓመታዊ ሪፖርት በሚያቀርቡበት ወቅት፣ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ በስተቀር ሁሉም የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች በስብሰባው መገኘት እንዳለባቸው ተደንግጓል።

ይህ ይሁን እንጂ ኦዲት ሪፖርቱ ሲቀርብ መገኘት ከነበረባቸው 22 ሚኒስትሮችና ሌሎች ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናት መካከል ጥቂቶች ብቻ እንደተገኙ መረጃዎች ያመለክታሉ። ይህ በመንግሥት ኃላፊዎች ደረጃ የኦዲት ግኝቱ ከፍተኛ ትኩረት እንዳልተሠጠው አመላካች ሊሆን ይችላል እላለሁ። ይህን ሃሳቤን የሚያጠናክርልኝም ዋና ኦዲተሯ ከኢቲቪ ጋር በነበራቸው ቆይታ ከኦዲት ግኝቱ ይልቅ ግኝቱ በሚዲያ መቅረቡ ስለሚያሳስባቸው ሚዲያዎች የኦዲት ግኝቱን በተገቢው ሁኔታ ተደራሽ አድርጉ ብለው ማሳሰባቸው ነው።

ከላይ እንደገለጽኩት የፌዴራል ዋና ኦዲተር ሪፖርትን አድምጦ ተገቢና ተከታታይ ርምጃ የመውሰድ ንቅናቄ ያስፈልጋል። ልክ እንደ ‹‹ኢትዮጵያ ታምርት›› አይነት የሆነ ስያሜ ተሰጥቶ የሚመለከታቸው አካላት ትኩረት ሰጥተው በቅንጅት ሊሠሩ ይገባል። ለቀጣይ ዓመት የተበጀተው በጀትም ትሪሊዮን ደርሷል፤ ይህን ትሪሊዮን በአግባቡ ወጪ ለማድረግ ከቀድመው በተለየ አካሄድ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ይገባል። ይህን ማድረግ ካልተቻለ ብልጽግናን ማምጣት አይቻልም።


ማህበራዊ

# ወጣቶች


ወጣት ባርኮት አሰፋ፣


ወጣት አሳዬ ተስፋዬ፣


ኢንጂነር አብዱልቃድር እድሪስ፣


የግንባታው ከፊል ገጽታ

## ደንቢ ሉጅና ፏፏቴ ፕሮጀክት - ለወጣቶች የፈጠረው ተስፋ

**ስምስም መንግሥቱ**

በጫካ ውስጥ ተደብቆ በኃይለኛ ድምጽ እያስገመገመ ቁልቁል ወደታች ይወርዳል። ንጣቱም የተገመደ ጥጥ ይመስላል። ሌላኛው ጢስ ዓባይ በየት በኩል መጣ ብዬ በአግራሞት እያየሁ ውሽፍሩን ልብ አላልኩትም። ከድንጋይ ጋር እየተላተመ የሚረጨው ውሃ ልብሴን አርሶታል። አካባቢውንም አርጥቦታል።

አረንጓዴ ከለበሰው ከአካባቢው ገጽታ ጋር ተዳምሮ ቀልብ ይይዛል። ድንቅ የሆነ የተፈጥሮ ፀጋ የተላበሰ አካባቢ። ቤንች ሸካ ዞን ድምቀት ስለሆነው ደንቢ ወንዝ ነው የምነግራችሁ። ይህ ድንቅ የተፈጥሮ ፀጋ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ቤንች ሸካ ዞን ውስጥ ነው የሚገኘው።

ለዘመናት በጫካ ውስጥ የሚፈሰው የደንቢ ወንዝ በገበታ ለትውልድ ዐሻራ ተገልጧል። መስህብ ሆኖ ቱሪስቶችን ለመሳብ፣ በፀጋውም የአካባቢውን ማህበረሰብ በኢኮኖሚ ተጠቃሚ ለማድረግ በዚያው ደንቢ ወንዝ ላይ ደንቢ ሎጅና ፏፏቴ የሚል ስያሜ የተሰጠው መዝናኛ እየተገነባ ነው። በአካባቢው ላይ ግንባታው እንዲከናወን ተነሳሽነቱን የወሰዱት የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይ አሕመድ ናቸው።

በደንቢ ሎጅና ፏፏቴ ፕሮጀክት ግንባታ ወጣቶች በተለያየ ሥራ በስፋት ተሠማርተዋል። በሥራው ላይ ካገኘናቸው መካከል ወጣት ባርኮት አሰፋ አንዷ ናት። ጠይም፣ አጠር ያለች፣ የደስደስ ያላት። ፈገግታዋና ሳቋ የሚጋባ፣ ቅልጥፍናዋም የሚስብ መልካምነቷ የበዛ ፍልቅልቅ ወጣት ናት። ባሬላ ተሸክማ ሥራዋን ስታቀላጥፍ አብረዋት የሚሠሩትን ጭምር በሥራ ታነቃቃለች።

ወጣት ባርኮት እኛ ስናገኛት በግንባታው ሥራ ሶስተኛ ወሯን ደፍና ነበር። የሥራ ድርሻዋ ለግንበኞች የሚያስፍልገውን ግብዓት በባሬላ ማቅረብ፣ ቀድመው የተገነቡትን ውሃ ማጠጣት ነው። እርስዋ እንዳለችው እንዲህ ያለው የፕሮጀክት ሥራ እንኳን ለእርስዋ ለአካባቢውም አዲስ ነው። እንዲህ ያለ የፕሮጀክት ሥራ ባለመኖሩ የቀን ሥራም በአካባቢው ላይ አልተለመደም። ለዚህም ነው እርስዋን ጨምሮ የአካባቢው ወጣቶች ለመሳተፍ ፍላጎት ያሳዩት።

ሥራውን ስትጀምር ከብዷት ነበር። በሂደት ግን ለምዳዋለች። ሥራውንም እየወደደችው ነው። እግረመንገዷንም ሥለግንባታ የተለያየ እውቀት እንዲኖራት ዕድል እየተፈጠረላት ነው። የቤተሰብን እጅ ከማየት የራስን ገቢ መፍጠር አንዱ ጥቅም ሆኖ አግኝታዋለች። በኢኮኖሚም በሙያም ተጠቃሚ መሆኗ አስደስቷታል። በጊዜ ቆይታም ባለሙያዎች የሚሠሩትን ሁሉ መሞከር ጀምራለች። ‹‹ማን ያውቃል አንድ ቀን የግንባታ ባለሙያ ሆኗ ትላልቅ ፕሮጀክቶችን በመያዝ ልሠራ የምችልበት አጋጣሚ ሊፈጠር ይችላል›› ስትልም ተስፋዋን ገልጻልናለች።

ወጣት ባርኮት፤ አብሲኒያ ከተባለ የግል ኮሌጅ በእስተዳደር (ማኔጅመንት) ከተመቀረች ገና አጭር ጊዜ ነው። የተመረቀችበት የትምህርት ዘርፍና አሁን የተሰማራችበት የሥራ ዘርፍ የተለያዩ ናቸው። ሥራውም የጉልበት ሥራ ነው። ወጣት ባርኮት በግንባታው ውስጥ ለመሥራት የተለያዩ ምክንያቶች እንዳሏት ትገልጻለች።

እርስዋ እንዳለችው በተማረችው የትምህርት ዘርፍ ሥራ እስኪታገኝ ማንኛውንም ሥራ መሥራቱ ጥሩ ነው የሚለው አንዱ ምክንያቷ ነው። ፕሮጀክቱ ለአካባቢው አዲስ ከመሆኑ ጋር ተያይዞም ግንባታው ተጠናቅቆ ወደ ሥራ ሲገባ በተማረችው የትምህርት ዘርፍ የመቀጠር ዕድል እንደሚኖራትም ተስፋ አድርጋለች።

በግንባታው ዘርፍም እግረመንገድ ተሞክሮ ማግኘትም ሌላው አማራጭ ነው። በግንባታው በሙያ ልምድ ያላቸው በእድሜም ከፍ ያሉ እንዲሁም ከተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍል የሚገኙበት መሆኑ የሥራ ባህልን ጨምሮ የተለያዩ ተሞክሮዎችን መቅሰም እንዳስቻላትም ገልጻለች። ዘመድም አፍርቻለሁ ትላለች። በሥራ አጋጣሚ ወደሌላ አካባቢ የመሄድ እድሉን ብታገኝ እንኳን እንደማትቸገር ነው የተናገረችው። ይህን ሁሉ ዕድል ማግኘት መቻሏ እድለኛ እንደሆነች ይሰማታል።

ወጣት ባርኮት ስለፕሮጀክቱ ምን ያህል ግንዛቤ እንዳላትም ጠይቀናት፤ ፕሮጀክቱ ለመዝናኛ የሚውል በተለይም ከተለያዩ የዓለም ሀገራት ቱሪስቶችን በመሳብ ጥቅም እንዲሰጥ ተደርጎ የሚከናወን እንደሆነ ነው የገለጸችው። በተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች ብዙ ቱሪስቶች ለጉብኝት እንደሚሄዱ መረጃው አላት። አሁን ደግሞ እርስዋ በምትኖርበት አካባቢ ለቱሪስት መስህብ የሚሆን ግንባታ መከናወኑ አስደስቷታል።

ወጣት ባርኮት እንዳጫወተችን፤ የፕሮጀክት ግንባታው የሚከናወንበት ስፍራ ቀደም ሲል ደን ነው የነበረው። ደኑ ስለሚያስፈራ ማንም ወደ አካባቢው አይሄድም። ደንቢ በርቀት ነው የሚታወቀው። ደንቢ ላይ እንዲህ ያለ ፕሮጀክት ይሠራል የሚል እምነትም ተስፋም አልነበረም። ይህ በመሆኑ እርስዋ ብቻ ሳይትሆን ሌሎች የአካባቢው ተወላጆች በተለይም ወጣቶች ደስተኛ እንደሆኑ እና በተለያየ አጋጣሚ ሲገናኙ ስለፕሮጀክቱ ሲያወሩ መስማቷንም አጫውታናለች። ወጣቶች በማህበር ተደራጅተው በተለያየ ሥራ ላይ ለመሠማራት የሚያስችል ተስፋ የሚሰጥ ፕሮጀክት እንደሆነም ገልጻለች።

ሌላው በግንባታ ሥራው ላይ ያገኘነው ወጣት አሳዬ ተስፋዬ ይባላል። በሥራው ላይ ከአምስት ወር በላይ ሆኖታል። በትምህርቱ በተለያየ ምክንያት ከስምንተኛ ክፍል በላይ መቀጠል አልቻለም። ያለትምህርትና ሥራ ከባድ እንደነበርና በአካባቢው ይሄ ፕሮጀክት መኖሩ እንደጠቀመው ይገልጻል።

በፕሮጀክቱ ውስጥ አርማታ ከማቡካት ጀምሮ የተለያዩ ሥራዎችን እየሠራ እንደሆነ የገለጸልን ወጣት አሳዬ፤ ቀደም ሲል አርማታ በሰው እጅ ይቦካ እንደነበርና በኋላ ላይ ግን በማሽን ማቡካት እንደተጀመረ ያስረዳል።

በሰው ጉልበትና በማሽን ማቡካት ያለውን ሰፊ ልዩነት ግንዛቤ ከመያዙ በተጨማሪ የሰውን ድካም የሚያቀል፣ ጊዜንም የሚቆጥብና ብክነትን የሚያስቀር ቴክኖሎጂ መኖሩን ያወቀው በፕሮጀክቱ ውስጥ ሲሠራ መሆኑንና እውቀትም እንዳገኘበት ተናግሯል።

ፕሮጀክቱ በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት በአካባቢው ላይ ትልቅ ለውጥ የሚያመጣ እንደሆነ ተገንዝቧል። በፕሮጀክቱ ውስጥ ተቀጥሮ በሚያገኘው ገቢ እና በሥራው አጋጣሚ ባገኘው እውቀት ተጠቃሚ ከመሆኑ በተጨማሪ በገበታ ለትውልድ ፕሮጀክት ሥራ የእርሱም ዐሻራ መኖሩ እንዳስደሰተው ነው የገለጸው። ፕሮጀክቱ ሲያልቅ እርሱም የሚዝናናበት እንደሆነም ተናግሯል።

ወጣት አሳዬ አካባቢው ላይ እንዲህ ያለ መዝናኛ ይኖራል ብሎ አስቦ እንደማያውቅ ነው የተናገረው። እርሱ እንዳለው የአካባቢው ወጣቶች ጊዜያቸውን የሚያሳልፉበትና የሚዝናኑበት የላቸውም። ከዚህ በኋላ እንዲህ ያሉ ፕሮጀክቶች እንደሚስፋፉ ተስፋ ያደርጋል። በተለይም ባለሀብቶች የሚሠሩበት ዕድል ቢመቻችላቸው ፕሮጀክቶቹ ሊሰፉ እንደሚችሉም ያምናል።

የደንቢ ሎጅና ፏፏቴ ፕሮጀክት ሥራ አስኪያጅም

> **ለዘመናት በጫካ ውስጥ የሚፈሰው የደንቢ ወንዝ በገበታ ለትውልድ ዐሻራ ተገልጧል። መስህብ ሆኖ ቱሪስቶችን ለመሳብ፣ በፀጋውም የአካባቢውን ማህበረሰብ በኢኮኖሚ ተጠቃሚ ለማድረግ በዚያው ደንቢ ወንዝ ላይ ደንቢ ሉጅና ፏፏቴ የሚል ስያሜ የተሰጠው መዝናኛ እየተገነባ ነው**

እንዲሁ ወጣት ነው። ኢንጂነር አብዱልቃድር እንዲሪስ ይባላል። እርሱም በገበታ ለትውልድ በሚከናወነው በዚህ ፕሮጀክት ተሳታፊ መሆኑ፣ እንዲህ ከከተማ ርቆ በሚገኝ ፕሮጀክት ላይ መሥራቱ ያሳደረበትን ስሜት ገልጾልናል።

‹‹ፕሮጀክቱ ከስያሜው እንደምንረዳው ወጣቱን ማዕከል ያደረገ ነው። ወጣቱ በተሠራው መዝናኛ ወይንም ሥራ መጠቀም ብቻ ሳይሆን፣ በሥራውም ተሳታፊ መሆን አለበት። የራሱንም ዐሻራ ማኖር ይጠበቅበታል። በተለያዩ አካባቢዎች የሥራ ልምዶች ሲኖሩት ሰፋ ያለ እውቀት ይኖረዋል።

እኔም ደንቢ ሎጅና ፏፏቴ ፕሮጀክት ሥራ ላይ ለመሳተፍ ስወስን ወደፊት ሰፋ በሆኑ ፕሮጀክቶች ላይም ለመሥራት የሚያስችል እድል ለማግኘትና በተለይም ገበታ ለትውልድ ላይ ዐሻራም እንዲኖረኝ ነው። አሁን የምገኝበት ሥራ ተነሳሽነትንም ፈጥሮልኛል።›› በማለት አስረድቷል።

ከከተማ ርቀው በሚገኙ አካባቢዎች ወጣ ብሎ መሥራቱ ምን እንደሚመስል፣ ያለውን ፈተናና ጫና ተቋቁሞ ማለፍና መልካም ነገሮችንም ማየት እንደሚያስፈልግም ወጣት አብዱልቃድር ይገልጻል። ደንቢ ሎጅና ፏፏቴ ፕሮጀክት ሥራ ከጀመረ ጀምሮ ከአካባቢው ርቆ እንዳልሄደና ውሎውና አዳሩ በፕሮጀክቱ ሥራ ላይ እንደሆነ ነው የነገረን።

ኢንጂነር አብዱልቃድር ደንቢ ሎጅ ፏፏቴ ፕሮጀክት የመጀመሪያው አይደለም። በተለያዩ አካባቢዎች በተከናወኑ ወደ አራት የሚሆኑ ፕሮጀክቶች ላይ በኃላፊነት ሠርቷል። ከአምቦ ዩኒቨርሲቲ በ2011ዓም ነው በሲቪል ምህንድስና ነው የተመረቀው።

ስለደንቢ ሎጅ ፏፏቴ ፕሮጀክት አጠቃላይ ሥራ በተመለከተ ኢንጂነር አብዱርቃድር እንደገለጸው፤ ፕሮጀክቱን በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ለማጠናቀቅ የታቀደ ሲሆን፣ ለፕሮጀክቱ የተያዘው በጀትም ወደ 180 ሚሊዮን ብር ነው። ገንዘቡ የፕሮጀክቱ ማጠናቀቂያ ሆኖ ግን አይታሰብም። የፕሮጀክቱ ግንባታ ወደ 45 በመቶ ደርሷል። የፕሮጀክቱ አማካሪና ኢንጂነሪንጉን የያዘው ጉባላፍቶ የተባለ ድርጅት ሲሆን፣ ተቋራጩ ደግሞ ራስመስ አዲስ የተባለ ኩባንያ ነው። ሚድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ ደግሞ ተቋራጭም ተቆጣጣሪም ሆኖ እየሠራ ይገኛል።

ደንቢ ወንዝ ወይንም ሐይቅ ዳርቻ ላይ እየተገነባ የሚገኘው ደንቢ ሎጅና ፏፏቴ፤ የመሰብሰቢያ አዳራሽ ጨምሮ ፣ በአንድ ጊዜ ከ 155 ሰዎች በላይ የማስተናገድ አቅም ያለው ካፌና ሬስቶራንት እንዲሁም በተለያየ ደረጃ የሚገኙ ማረፊያ ክፍሎች አለው። ሁለት ባለሁለት መኝታ፣ ሁለት ባለሶስት መኝታ 11 ባለአንድ መኝታ፣ ከነዚህ ውስጥም ዘጠኙ ሁለት ሁለት ክፍሎች ሁለቱ ደግሞ አንዳንድ ክፍሎች ይኖራቸዋል።

ከግንባታው ተጠናቅቆ አገልግሎት ላይ ሲውል ለደንምበኞች የሚቀርብ ምግብ በአካባቢው ላይ ምቹ እንዲሆን ጎን ለጎን ደንቢ ሐይቅ ላይ የአሣ እርባታ የሚከናወንበት ሁኔታም ለማመቻቸት ታቅዷል።

በግንባታ ሥራ የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶች እንደሚኖሩ ይጠበቃል። በዚህ ረገድ ስላለው ሁኔታና ተግዳሮቶችንም ተቋቁሞ ሥራውን ለማከናወን እየተደረገ ስላለው ጥረት የፕሮጀክቱ ሥራ አስኪያጅ አብዱልቃድር እንደገለጸልን፤ በእቅዱ መሠረት ለመሄድ ተግዳሮት የሆነው አንዱ አካባቢው ዝናባማ በመሆኑ በዝናብ ወቅት ሥራ ይቋረጣል። ለግንባታ የሚውል ድንጋይ፣ ጠጠር፣ አሸዋ የመሳሰሉ ግብዓቶች በአካባቢው ላይ አለመገኘቱ ሌላው ተግዳሮት ነው። ከርቀት ቦታ ተጓጎዞ ነው የሚቀርበው።

የወባ በሽታም በስፋት በመኖሩ ሠራተኞች ታመው ከሥራ ይቀራሉ። በነዚህ ምክንያቶች እየተፈጠሩ ያሉ መዘግየቶችን የእርፍት ቀናቶችን ጨምሮ እስከ ምሽት ድረስ በመሥራት የባከነውን ጊዜ በማካካስ ነው ችግሮችን ለመቋቋም ጥረት እየተደረገ ያለው።

ከሥራ ዕድል ፈጠራ አኳያም በግንባታ ፕሮጀክቱ ሥራ ላይ በስፋት እየተሳተፉ የሚገኙት የአካባቢው ወጣቶች ሲሆኑ፣ ካለው የሰው ኃይልም ወደ ሁለት መቶ የሚሆኑት የአካባቢው ወጣቶች ናቸው። ከፍ ባለ ሙያ ላይ ልምድ ያላቸው ከአዲስ አበባ ከተማ በማስመጣት እንዲሠሩ እየተደረገ ቢሆንም በአካባቢው ላይ መጠነኛ የሆነ እውቀት ያላቸው ሲገኙ በሥልጠና እና ልምድ ካላቸውም የእውቀት ሽግግር በማድረግ ሙያ በሚጠይቅ ሥራ ላይ እንዲሳተፉ እየተደረገ ነው። ፕሮጀክቱ የቀን የሥራ ዕድል ብቻ ሳይሆን፣ በግንባታው ዘርፍ ባለሙያም እየፈጠረ ነው። በገበታ ለትውልድ የተከናወኑ ፕሮጀክቶች በተለይም በቱሪዝም ኢንዱስትሪው ላይ ከፍተኛ መነቃቃት እየፈጠሩ እንደሆነ ይታወቃል።

# የምድር በረከት

## ዩኒቨርሲቲው በማዕድን ዘርፉ ያለው አበርክቶ

**ወርቅነሽ ደምሰው**

መንግሥት ከአምስቱ ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ምሰሶ ለሆነው የማዕድን ዘርፍ ትልቅ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ ይገኛል። ይሁን እንጂ ዘርፉ ገና ያልተነካ፣ በብዙ ያልተሠራበትና በአግባቡ ያልተመራ እንደመሆኑ የሠለጠነና ብቁ የሆነ የሰው ኃይል የሚያስፈልገው እንደሆነም ይነገራል።

በተለይ ዘርፉ እውቀትና ብቃት ባለው የሰው ኃይል እንዲመራ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትም ሚናቸው የጎላ ነው። በዚህም በዘርፉ የሰለጠነ ብቁ የሰው ኃይል በማፍራት በጥናትና ምርምር የመደገፍ ሥራዎች እንዲሠሩ ይጠበቃል። ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አንዱ የሆነው ባህርዳር ዩኒቨርሲቲም ይህንኑ ተግባራዊ እያደረገ ይገኛል። የማዕድን ዘርፉን ከመደገፍ አንጻር የሠራቸው በርካታ ሥራዎች እንዳሉም ተመላክቷል።

ዶክተር አሸብር ሰውአለ የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ እስኩል ኦፍ እርዝሳይንስ ዳይሬክተር ናቸው። እሳቸው እንደሚሉት፤ በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ እስኩልኦፍ እርዝሳይንስ የተቋቋመበት ዋና ዓላማ በማዕድናና ውሃ ሀብት ላይ ትኩረት አድርጎ እንዲሠራ ታስቦ ነው። ከእነዚህ ውስጥ አንዱ የማዕድን ዘርፍ እንደመሆኑ በተለይም በአማራ ክልል ያሉ ማዕድናት ላይ ትኩረት አድርጎ እየሠራ ይገኛል።

ቀደም ሲል በ2010 ዓ.ም በክልሉ የሚገኙ የኦፓል ማዕድናት በተመለከተ በአምስት ወረዳዎች ጥናት በመካሄድ ያለው የኦፓል አቅምና የጂኦሎጂካል አቀማመጥ የሚያሳይ ካርታ በመሥራቱን አሸብር (ዶክተር) ያመላክታሉ። ቀጥሎም የክልሉ ማዕድን ሀብት ለማልማት የሚያስችል ፍኖተ ካርታ ተሠርቶ እንዳለቀ በሰሜኑ የሀገሪቷ ክፍል በነበረው ጦርነት ምክንያት ሥራው እንደተቋረጠ ይናገራሉ።

በፍኖተ ካርታ ከተለዩት ችግሮች አንዱ በክልሉ ማዕድን ዘርፍ የመዋቅር ችግር እንደነበር አንስተዋል። የመዋቅር ችግሩን ለመፍታት የክልሉ ማዕድን የሚመራው አካል በቢሮ ደረጃ እንዲቋቋም የቀረበበት ሁኔታ ስለነበር አሁን ላይ ጥናቱ ተቀባይነት አግኝቶ የክልሉ ማዕድን ኤጀንሲ በቢሮ ደረጃ እንዲያድግ ተደርጓል። ፍኖተ ካርታው ለክልሉ ካቢኔ ቀርቦ ባይጸድቅም ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑን ጠቅሰው፤ አሁንም ፎኖተ ካርታው አሁናዊ ሁኔታዎችን እንዲያካትት ተደርጎ ማሻሻል ተሠርቶለት የተጠናቀቀ በመሆኑ በቅርቡም ለሚመለከታቸው አካላት የሚቀርብ ይሆናል ሲሉ ተናግረዋል።

‹‹በፍኖተ ካርታ እንደተመላከተው የክልሉ የማዕድን ሀብት እንደሌላው ዘርፍ ባለሀብቶች ተንደርድሮ የሚገባበት አይደለም›› የሚሉት አሸብር (ዶክተር)፤ ማዕድን ማልማት በጣም አደጋ እንዳለው መገንዘብን የሚጠይቅ ነው። አደጋውም የማዕድን ሀብቱን ለማልማት የሆነ ቦታ ላይ ማዕድን አገኛለሁ ተብሎ ብዙ ኢንቨስትመንት ወጥቶበት ምንም ላይገኝ ይችላል፤ ይህም በጥንቃቄ መመራት እንዳለበት ያሳያል። የሌሎች ሀገራት ተሞክሮ እንደሚያሳየው እንደ መንግሥት በተለይ የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ ተቋም የማዕድን አለኝታ ቦታዎች (minerals potential area) በመለየት ወርቅ፣ ብረት እና መሰል ማዕድናት የትኞቹ አካባቢዎች ላይ ይገኛሉ የሚለው አጥንቶ ቅድሚያ ማሳየት ይጠበቅበታል። ነገር ግን አሁን ባለው ሂደት የሀገሪቱ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ ኢንስቲትዩት በብዛት ወርቅ የሚገኝባቸው ቦታዎች ላይ ብቻ ተወስኖ ነው አመላካች ካርታ የሠራው ሲሉ ያስረዳሉ።

በክልሉ ያለው የጂኦሎጂካል ካርታ በራሱ በጣም ደካማ ስለሆነ ይህ ክፍተት ለመሙላት ጥናቶች መጠናት እንዳለባቸው ያመላክታሉ። ዩኒቨርሲቲውም ከክልሉ የማዕድን ቢሮ ጋር የሚሠራቸው ሥራዎች እንዳሉ ሆነው በራሱ በጀት ሥራዎችን እየሠራ መሆኑን ይገልጻሉ። ቀደም ሲል ከተጀመሩት የኦፓል ማዕድን ጥናት በተጨማሪ በመርጦለማርያም አካባቢ ለሲሚንቶ ግብዓት የሚውል የድንጋይ ከሰል እና የብረት ማዕድናት ጥናት አጥንቶ ሰነዱን ለማዕድን ቢሮ ማስረከቡን ጠቅሰው፤ ቢሮውም ጥናቱን መሠረት በማድረግ በእነዚህ ዘርፍ ባለሀብቶች እንዲሠማሩበት ያደረገ መሆኑን ተናግረዋል።

ከዚህ ባሻገርም ወንበርማ ጉመር በሚባል አካባቢ የወርቅ ማዕድን ጥናት ተካሂዷል። ዳንጉ ወረዳ ላይ የጂኦሎጂካል ካርታ ተሠርቷል። እብናት ወረዳም እንዲሁ የብረት ማዕድናት ጥናት ተካሂዷል። በአጠቃላይ በክልሉ ማዕድን ቢሮ በጀት አምስት ፕሮጀክቶች ተሠርተዋል። እነዚህ ሦስቱን ፕሮጀክቶች በዚህ ዓመት የተጠናቀቁ ለቢሮ የተሰጡ ሲሆን የኦፓልና የመርጦለማርያም አካባቢ ጥናት በባለፈው ዓመት የተካሄዱ መሆኑን አንስተዋል።

> **በፍኖተ ካርታ የእውቀት ክፍተት አንዱ ተግዳሮት እንደሆነ ተመላክቷል። የእውቀት ክፍተቱን ለመሙላት በክልሉ ማዕድን ቢሮ ያሉትን ባለሙያዎች ከዩኒቨርሲቲ ጋር በማቀናጀት ልምድና እውቀት እንዲያገኙ፣ የተሠራው ሥራም በቀላሉ እንዲረዱትና እንዲተነትኑ ለማድረግ ጥረት እየተደረገ ነው**

ፕሮጀክቶቹ የተጀመሩ ከሦስትና ከሁለት ዓመት በፊት ሲሆን ተጠናቅቀው የተረከቡት ዘንድሮ ነው ያሉት አሸብር (ዶ/ር)፤ በተደረጉት ጥናቶች የማዕድን ዘርፉ ለማልማት መሠረት የሆኑ አመላካቾችን ማሳየት እንደሚያስችሉ ገልጸዋል። ለአብነትም አንድ ወረዳ ላይ አንድ ባለሀብት የወርቅ ማዕድን እንዲፈልግ ብናደርግ ወርቅ ለማጥናት በጣም ብዙ ኢንቨስትመንት፣ ሳይንሳዊ ትንታኔና ጥናትና ምርምር ማድረግ ይጠበቅበታል። ይህ ደግሞ ባለሀብቱ ብዙ ወጪ አውጥቶ በዘርፉ ለመሰማራት ያለውን ፍላጎት ይቀንሳል። በመሆኑም ቅድሚያ በዘርፉ ያለውን አቅም የሚያሳይ ሳይንሳዊ ትንታኔና ጥናትና ምርምር ማድረግ የግድ ይላል።

‹‹በጂኦሎጂ ሳይንስ አንድ ማዕድን የት አካባቢ ከየትኞቹ አለቶች ጋር ሊገኝ ይችላል፤ ለምሳሌ ወርቅ ከምን አይነት አለቶች ጋር ሊገኝ ይችላል የሚለው የራሱ የሆነ ሳይንሳዊ አካሄድ አለው። ማዕድን ባለሀብት ስለሆንን ብር ስላለን ብቻ የምንሠራው ነገር ሳይሆን ሳይንሳዊ ምርምር የሚጠይቅ ነው›› ያሉት አሸብር (ዶ/ር)፤ ማዕድኑ የትኛው አካባቢ ላይ ይገኛል፤ ምን ያህል አቅም አለው የሚለው እርግጠኛ መሆን አይቻልም፤ በሳይንሳዊ ምርምር ግን ወርቅ ሊገኝበት የሚችል ቦታ ማመላከት ይቻላል። አዋጭነቱን በተመለከተ ግን ሌላ ጥናት የሚጠይቅ በመሆኑ በዘርፉ ለመሠማራት የሚፈልገው ባለሀብት አዋጭነቱን አጥንቶ ማዕድን ወደ ማውጣት ለመግባት ሁኔታዎችን ቀለል ያደርጋል።

ማዕድን መኖሩ ካልታወቀ ማዕድን የማውጣቱ ሥራ አደጋ ያለውና ማዕድን ሊገኝም ላይገኝም ይችላል። ነገር ግን መጀመሪያው መንግሥት አጥንቶ አመላካች ቦታውን ካሳየ ባለሀብቱ ደግሞ ማዕድን አላቸው ተብለው የተለዩ ቦታዎች ላይ ኢንቨስት ማድረግ ይችላል። ይህም አደጋውን የሚቀንስ ይሆናል። ያም ሆኖ ማዕድን ማውጣት ከፍተኛ የኢንቨስትመንት አቅምን ይጠይቃል ሲሉ አብራርተዋል።

‹‹በተለይ ማዕድን ማውጣት ላይ መሠረታዊ የሆነ ጂኦሎጂካል ካርታ ካለ ማዕድን ያለበትን ቦታ መለየት ይቻላል። በክልሉ አቅም የተለዩ ቦታዎች በአብዛኛው ትኩረት ተሠጥቷቸው የተሠሩ ሲሆን በዚህ መሰረት አመላካች ጂኦሎጂካል ካርታ መሥራት ተችሏል›› ብለዋል።

ዩኒቨርሲቲው በራሱ በጀት በሚያሠራው የማዕድን ጥናት አማካኝነት በወሎ የማንጋኒዝ እና ቡሬ የወርቅ ማዕድናት ላይ ጥናት ያደረገ ሲሆን የጥናቱም ውጤት ለክልሉ ማዕድን ቢሮ መስጠቱን አመላክተዋል። ‹‹ከማዕድን ቢሮ ጋር የተሻለ ግንኙነት ስላለን ብዙ ሥራዎች አብረን እየሠራን ነው። ለአብነትም በነዳጅ ማዕድን ወሎ ወረኢሉ አካባቢ ጥናት የተካሄደ ሲሆን የተገኘው ውጤት ገለጻ ተደርጎል። ዩኒቨርሲቲው እንደዚህ አይነት ተያያዥነት ያላቸው ፕሮጀክቶችን በመሥራት ለቢሮ እያቀረበ ይገኛል›› ሲሉ አስረድተዋል።

እንደ እሳቸው ማብራሪያ፤ በአሁኑ ወቅት ደግሞ ከማዕድን ቢሮ በተደረገ ስምምነት መሠረታዊ የጂኦሎጂካል ካርታ እየተሠራ ነው። የአለቱን አይነት፣ ስርጭት እና ሁኔታን በማጥናት በዚህ መነሻነት ደግሞ በክልሉ ምን አይነት ማዕድናት ሊገኙ ይችላሉ የሚለውን ጭምር አመላካች ካርታ ይሠራል። ይህ ሥራ ለአንድ ዓመት ያህል የሚቆይ ሲሆን፤ ሥራው በየጊዜው የተለያዩ ሂደቶች መሻገር ይጠበቅበታል። አሁን ላይ በቅድሚያ የሳተላይት ምስሎች፣ ከዚህ ቀደም ከተሠሩ ሥራዎችና ከኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ በመውሰድ ይሠራሉ። በመቀጠልም የመጀመሪያ ዳሰሳ ስራ የሚሰራ ሲሆን፤ ከዚያም በእቅዱ መሰረት በጥልቀት ያለውን ጂኦሎጂካል ካርታ ሥራ ይሠራል። በዚህ ሂደት የተገኘው ናሙና ሀገር ውስጥ የሚሠራውን ሀገር ውስጥ እንዲሠራ፤ ውጭ ሀገር የሚላከውን ወደ ውጭ አገር በመላክ ትንተናው ተሠርቶ ካለቀ በኋላ ሪፖርት በማድረግ ካርታው የሚሠራ ይሆናል።

እስካሁን የተሠራው አብዛኛው ሥራ የጂኦሎጂካል ካርታ ነው፤ በማዕድን ፍለጋ ዙሪያ የተወሰኑ ሥራዎች መሠራታቸውን አመላክተዋል። የማዕድን ጥናት የተለያየ ሂደት ስላለው ማዕድኑ ወዳለበት አካባቢን እያጠበቡ አለኝታ ወደሆነበት አካባቢ መሄድን የሚጠይቅ እንደሆነ ይገልጻሉ። ‹‹ይህም በዞኑ የወርቅ ማዕድን አለ ካልን፤ ያን የወርቅ ክምችቱ ምን ያህል ነው የሚለውንም ማየት ይቻላል›› ብለዋል።

‹‹በማንኛውም አለት ውስጥ መጠኑ በጣም ጥቂት ሊሆን ይችላል እንጂ ወርቅ አለ›› የሚሉት አሸብር (ዶ/ር)፤ ‹‹አንድን ድንጋይ ተፈጭቶ ሂደቶችን አልፎ አዋጭ የሚሆነው እንደ ገበያው የወርቅ ዋጋ ቢለያይም በአንድ ቶን አለት ውስጥ 1 ነጥብ 5 ግራም ወርቅ ካለ አዋጭ ነው ማለት ነው። ከዚህ በታች ከሆነ ያንን ወርቅ ለማውጣት የሚደረገው ጥረት አዋጭ ላይሆን ይችላል›› ሲሉ አስገንዝበዋል።

የዳሰሳ ጥናት በተደረገባቸው አካባቢዎች የማዕድን አለኝታነትና ያለውን አቅም በመለየት አመላካቾች የተጠቆሙበት ሁኔታ መኖሩን ይገልጻሉ። ለምሳሌ ወንበርማ አካባቢ በተደረገው ጥናት ወርቅ መኖሩን አመላካቾች ተገኝተዋል። ነገር ግን ምን ያህል የወርቅ ክምችት በምን ያህል ርቀት የሚለውን ለማወቅ ጥልቀት ያለው ጥናት ማድረግን ይጠይቃል። በተለይ ውድ ለሆነ እንደ ወርቅ አይነት ማዕድናት ላይ ጥልቅ ጥናት ሳይደረግ እንደዚህ አይነት ክምችት አለን ማለት እንደማይቻል አስታውቀዋል።

የጂኦሎጂካል ካርታ መሠራቱ ዋና ዓላማ ክልሉ ላይ በማዕድን ዘርፍ ለመሠማራት የሚፈልግ ባለሀብት ሲመጣ የትቦታ ላይ ኢንቨስት ማድረግ እንደሚችል ለማመላከት ታስቦ ነው። ያሉት አሸብር (ዶ/ር)፤ ማዕድኑ የት ቦታ ላይ በተሻለ መልኩ ይገኛል የሚለው በሚያጠና እንደመሆኑ ጂኦሎጂካል ካርታው መሥራቱ ለክልሉ የሚሰጠው ጠቀሜታ ብዙ እንደሆነ ይናገራሉ። ሥራው ሲያልቅ ክልሉ ማዕድን አመላካች ካርታ ይኖረዋል ማለት ስለሆነ አንድ ባለሀብት የብረት ማዕድን ላይ ኢንቨስት ማድረግ እፈልጋለሁ ብሎ ቢመጣ ክልሉ የብረት ማዕድን ያለበት አካባቢ በቀላሉ በመጠቆም ባለሀብቱ ቦታው ላይ በመሄድ ጥልቅ ጥናት እንዲያደርግና አዋጭ ከሆነ እንዲሠማራበት ለማድረግ ያስችለዋል። ነገር ግን እንደዚህ አይነት ጥናቶች ከሌሉ ባለሀብቱ የት ቦታ ላይ ኢንቨስት እንደሚያደርግ ስለማያወቅ ተግዳሮት ይሆንበታል ብለዋል።

ቀደም ሲል በተሠራው ፍኖተ ካርታ እንደተመላከተው የክልሉን ማዕድን ለማወቅ የክልሉ መሠረታዊ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ አለመሥራት እንደተግዳሮት ተወስዷል። ያሉት አሸብር (ዶክተር)፤ በክልሉ ማዕድን አመላካች ለመሥራት የተሞከረ ሙከራ ቢኖርም እንኳን በደንብ ተቀናብሮ በጥናት ተደግፍ የተሠራ የክልሉ ማዕድን አመላካች ካርታ የለም። በመሆኑም ጂኦሎጂካል ካርታ መሠራቱ በዋነኛነት ይህን ክፍተት ለመሙላት ያስችላል። ሌላኛው የመዋቅር ችግር እንደነበር የተመላከተ ሲሆን፤ አሁን ላይ በተወሰነ መልኩ የተፈታበት ሁኔታ መኖሩን ይገልጻሉ።

በፍኖተ ካርታ የእውቀት ክፍተት አንዱ ተግዳሮት እንደሆነ ተመላክቷል። የእውቀት ክፍተቱን ለመሙላት በክልሉ ማዕድን ቢሮ ያሉትን ባለሙያዎች ከዩኒቨርሲቲ ጋር በማቀናጀት ልምድና እውቀት እንዲያገኙ፣ የተሠራው ሥራም በቀላሉ እንዲረዱትና እንዲተነትኑ ለማድረግ ጥረት እየተደረገ ነው። በተጨማሪ የአቅም ችግር ለመቅረፍ የአጭር ጊዜ ሥልጠናዎች እና የእውቀት ሽግግር እንደሚያደርጉ ተናግረዋል።

የማዕድን ዘርፉ ዋነኛ ዓላማ ያሉትን የማዕድን ሀብቶች ተጠቅሞ የክልሉን ሕዝብ ከድህነት ማላቀቅ ነው ያሉት አሸብር (ዶ/ር)፤ ይህም በክልሉ በማዕድን ዘርፍ ኢንቨስት ማድረግ የሚፈልግ ባለሀብት በጥናት የተደገፈ መረጃ እንዲያገኝ እድሉ መፍጠር ነው። ‹‹በአጠቃላይ ክልሉንም ሆነ ሀገር ሊያሳድግ የሚችል ኢንቨስትመንት ሲመጣ የተሟላ ሳይንሳዊ የሆነ መረጃ ማቅረብ አለብን›› ሲሉ አስገንዝበዋል።

እሳቸው እንደሚሉት፤ ለማንኛውም የማዕድን ኢንቨስትመንት መሠረታዊ ጂኦሎጂካል ካርታ መሠራት ያስፈልጋል። ጂኦሎጂካል ካርታ ካለ ባለሀብቱ ወደ ቀጣይ ሂደት በቀላሉ ሊሄድ ይችላል። እንደክልል ያለው የማዕድን ሀብት ለማወቅ ጥናት በማጥናት ስለሚያስፈልግ ዩኒቨርሲቲውም ባሉት ባለሙያዎች በመታገዝ ኃላፊነት ወስዶ የክልሉ የማዕድን ሀብት እንዲለማ የሚያስችሉ ሥራዎች እየሠራ ነው።

ማዕድን እንደሀገር ትኩረት የተሰጠው ዘርፍ በመሆኑም በክልሉ አሁን ላይ ጥሩ ጅማሮዎች አሉ የሚሉት አሸብር (ዶ/ር)፤ ዩኒቨርሲቲው በጥናት ሆነ በሳይንሳዊ ትንታኔም ያሉ ክፍተቶችን በመሙላት በማዕድን ኢንቨስትመንት ባዶ የነበረው መረጃ እያሟላ መሆኑን ያመላክታሉ። ‹‹ማዕድን በአንዴ ተሰርቶ የሚያልቅ ባለመሆኑ በሂደት የክልሉን ሙሉ መሠረታዊ የሆነ የጂኦሎጂካል ካርታ እና የማዕድን አለኝታ ኖሮ ለማዕድን የተመቻቸ አካባቢያዊ እንፈጥራለን›› ሲሉ ተናግረዋል።

ዩኒቨርሲቲው የአካዳሚክና የምርምር ተቋማት እንደመሆኑ በላብራቶሪ በኩል ያለውን ክፍተት በመሙላት ለመደገፍ ባለፉት አራት ዓመታት ከ40 እስከ 50 ሚሊዮን ብር በላይ የሚያወጡ ላብራቶሪ ማሽኖች ገዝቶ መትከል ችሏል። በቀጣይ መሠረታዊ የሚባሉትን አስፈላጊ ቁሳቁሶች እያሟላ ለማዕድን ዘርፉ መፍትሔ መስጠቱን ይቀጥላል። የክልሉ ማዕድን ሀብት በማልማት ረገድ በላብራቶሪና በጥናት ድጋፍ እያደረገ ነው።

በተጨማሪም የአጭርና የረጅም ጊዜ ሥልጠናዎች በማዘጋጀት ለባለሙያዎች ይሰጣል። እንዲሁም በአካዳሚክ ትምህርት የመጀመሪያ ዲግሪ የጂኦሎጂ ትምህርት ዘርፍ የሚሰጥ ቢሆንም ትምህርቱ ማዕድን፣ የከርሰምድር ውሃው፣ አካባቢ እና ኢንጂነሪግ ያካተተ ጠቅለል ያለ ትምህርት የሚሰጥበት ነው። በቅርቡም ሁለተኛ ዲግሪ (በማስተር ደረጃ) በማሳደግ ኢኮኖሚክ ጂኦሎጂ ዘርፍ (በሚኒራል ዲፖዚት) ዘርፍ ትምህርት እንዲሰጥ ተደርጓል። ይህም በዘርፉ የሠለጠነና ብቁ የሰው ኃይል ለማፍራት ያስችላል።

‹‹በማዕድን ዘርፉ የሚሠሩ ሥራዎች ከዩኒቨርሲቲው ዓላማ ጋር አብሮ የሚሄዱና በክልሉ የማዕድን ቢሮ ተቀባይነት ያላቸው ናቸው። እኛም እንደዩኒቨርሲቲ በምንሠራው ሥራ የሚቀበለን ስላለ ደስተኞች ነን። በእውቀትና ክህሎት፣ በአጭርና ረጅም ሥልጠናዎች እና ጥናት እና በላብራቶሪ በኩል ድጋፍ በማድረግ አገልግሎት እየሠጠን ነው›› ሲሉ አስገንዝበዋል

# የምድር በረከት

# ዩኒቨርሲቲው በማዕድን ዘርፉ ያለው አበርክቶ

**ወርቅነሽ ደምሰው**

መንግሥት ከአምስቱ ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ምሰሶ ለሆነው የማዕድን ዘርፍ ትልቅ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ ይገኛል። ይሁን እንጂ ዘርፉ ገና ያልተነካ፣ በብዙ ያልተሠራበትና በአግባቡ ያልተመራ እንደመሆኑ የሠለጠነና ብቁ የሆነ የሰው ኃይል የሚያስፈልገው እንደሆነም ይነገራል።

በተለይ ዘርፉ እውቀትና ብቃት ባለው የሰው ኃይል እንዲመራ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትም ሚናቸው የጎላ ነው። በዚህም በዘርፉ የሰለጠነ ብቁ የሰው ኃይል በማፍራት በጥናትና ምርምር የመደገፍ ሥራዎች እንዲሠሩ ይጠበቃል። ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አንዱ የሆነው ባህርዳር ዩኒቨርሲቲም ይህንኑ ተግባራዊ እያደረገ ይገኛል። የማዕድን ዘርፉን ከመደገፍ አንጻር የሠራቸው በርካታ ሥራዎች እንዳሉም ተመላክቷል።

ዶክተር አሸብር ሰውአለ የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ እስኩል ኦፍ እርዝሳይንስ ዳይሬክተር ናቸው። እሳቸው እንደሚሉት፤ በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ እስኩልኦፍ እርዝሳይንስ የተቋቋመበት ዋና ዓላማ በማዕድናና ውሃ ሀብት ላይ ትኩረት አድርጎ እንዲሠራ ታስቦ ነው። ከእነዚህ ውስጥ አንዱ የማዕድን ዘርፍ እንደመሆኑ በተለይም በአማራ ክልል ያሉ ማዕድናት ላይ ትኩረት አድርጎ እየሠራ ይገኛል።

ቀደም ሲል በ2010 ዓ.ም በክልሉ የሚገኙ የኦፓል ማዕድናት በተመለከተ በአምስት ወረዳዎች ጥናት በመካሄድ ያለው የኦፓል አቅምና የጂኦሎጂካል አቀማመጥ የሚያሳይ ካርታ በመሥራቱን አሸብር (ዶክተር) ያመላክታሉ። ቀጥሎም የክልሉ ማዕድን ሀብት ለማልማት የሚያስችል ፍኖተ ካርታ ተሠርቶ እንዳለቀ በሰሜኑ የሀገሪቷ ክፍል በነበረው ጦርነት ምክንያት ሥራው እንደተቋረጠ ይናገራሉ።

በፍኖተ ካርታ ከተለዩት ችግሮች አንዱ በክልሉ ማዕድን ዘርፍ የመዋቅር ችግር እንደነበር አንስተዋል። የመዋቅር ችግሩን ለመፍታት የክልሉ ማዕድን የሚመራው አካል በቢሮ ደረጃ እንዲቋቋም የቀረበበት ሁኔታ ስለነበር አሁን ላይ ጥናቱ ተቀባይነት አግኝቶ የክልሉ ማዕድን ኤጀንሲ በቢሮ ደረጃ እንዲያድግ ተደርጓል። ፍኖተ ካርታው ለክልሉ ካቢኔ ቀርቦ ባይጸድቅም ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑን ጠቅሰው፤ አሁንም ፎኖተ ካርታው አሁናዊ ሁኔታዎችን እንዲያካትት ተደርጎ ማሻሻል ተሠርቶለት የተጠናቀቀ በመሆኑ በቅርቡም ለሚመለከታቸው አካላት የሚቀርብ ይሆናል ሲሉ ተናግረዋል።

‹‹በፍኖተ ካርታ እንደተመላከተው የክልሉ የማዕድን ሀብት እንደሌላው ዘርፍ ባለሀብቶች ተንደርድሮ የሚገባበት አይደለም›› የሚሉት አሸብር (ዶክተር)፤ ማዕድን ማልማት በጣም አደጋ እንዳለው መገንዘብን የሚጠይቅ ነው። አደጋውም የማዕድን ሀብቱን ለማልማት የሆነ ቦታ ላይ ማዕድን አገኛለሁ ተብሎ ብዙ ኢንቨስትመንት ወጥቶበት ምንም ላይገኝ ይችላል፤ ይህም በጥንቃቄ መመራት እንዳለበት ያሳያል። የሌሎች ሀገራት ተሞክሮ እንደሚያሳየው እንደ መንግሥት በተለይ የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ ተቋም የማዕድን አለኝታ ቦታዎች (minerals potential area) በመለየት ወርቅ፣ ብረት እና መሰል ማዕድናት የትኞቹ አካባቢዎች ላይ ይገኛሉ የሚለው አጥንቶ ቅድሚያ ማሳየት ይጠበቅበታል። ነገር ግን አሁን ባለው ሂደት የሀገሪቱ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ ኢንስቲትዩት በብዛት ወርቅ የሚገኝባቸው ቦታዎች ላይ ብቻ ተወስኖ ነው አመላካች ካርታ የሠራው ሲሉ ያስረዳሉ።

በክልሉ ያለው የጂኦሎጂካል ካርታ በራሱ በጣም ደካማ ስለሆነ ይህ ክፍተት ለመሙላት ጥናቶች መጠናት እንዳለባቸው ያመላክታሉ። ዩኒቨርሲቲውም ከክልሉ የማዕድን ቢሮ ጋር የሚሠራቸው ሥራዎች እንዳሉ ሆነው በራሱ በጀት ሥራዎችን እየሠራ መሆኑን ይገልጻሉ። ቀደም ሲል ከተጀመሩት የኦፓል ማዕድን ጥናት በተጨማሪ በመርጦለማርያም አካባቢ ለሲሚንቶ ግብዓት የሚውል የድንጋይ ከሰል እና የብረት ማዕድናት ጥናት አጥንቶ ሰነዱን ለማዕድን ቢሮ ማስረከቡን ጠቅሰው፤ ቢሮውም ጥናቱን መሠረት በማድረግ በእነዚህ ዘርፍ ባለሀብቶች እንዲሠማሩበት ያደረገ መሆኑን ተናግረዋል።

ከዚህ ባሻገርም ወንበርማ ጉመር በሚባል አካባቢ የወርቅ ማዕድን ጥናት ተካሂዷል። ዳንጓ ወረዳ ላይ የጂኦሎጂካል ካርታ ተሠርቷል። እብናት ወረዳም እንዲሁ የብረት ማዕድናት ጥናት ተካሂዷል። በአጠቃላይ በክልሉ ማዕድን ቢሮ በጀት አምስት ፕሮጀክቶች ተሠርተዋል። እነዚህ ሦስቱን ፕሮጀክቶች በዚህ ዓመት የተጠናቀቁ ለቢሮ የተሰጡ ሲሆን የኦፓልና የመርጦለማርያም አካባቢ ጥናት በባለፈው ዓመት የተካሄዱ መሆኑን አንስተዋል።

ፕሮጀክቶቹ የተጀመሩ ከሦስትና ከሁለት ዓመት በፊት ሲሆን ተጠናቅቀው የተረከቡት ዘንድሮ ነው ያሉት አሸብር (ዶ/ር)፤ በተደረጉት ጥናቶች የማዕድን ዘርፉ ለማልማት መሠረት የሆኑ አመላካቾችን ማሳየት እንደሚያስችሉ ገልጸዋል። ለአብነትም አንድ ወረዳ ላይ አንድ ባለሀብት የወርቅ ማዕድን እንዲፈልግ ብናደርግ ወርቅ ለማጥናት በጣም ብዙ ኢንቨስትመንት፣ ሳይንሳዊ ትንታኔና ጥናትና ምርምር ማድረግ ይጠበቅበታል። ይህ ደግሞ ባለሀብቱ ብዙ ወጪ አውጥቶ በዘርፉ ለመሰማራት ያለውን ፍላጎት ይቀንሳል። በመሆኑም ቅድሚያ በዘርፉ ያለውን አቅም የሚያሳይ ሳይንሳዊ ትንታኔና ጥናትና ምርምር ማድረግ የግድ ይላል።

‹‹በጂኦሎጂ ሳይንስ አንድ ማዕድን የት አካባቢ ከየትኞቹ አለቶች ጋር ሊገኝ ይችላል፤ ለምሳሌ ወርቅ ከምን አይነት አለቶች ጋር ሊገኝ ይችላል የሚለው የራሱ የሆነ ሳይንሳዊ አካሄድ አለው። ማዕድን ባለሀብት ስለሆንን ብር ስላለን ብቻ የምንሠራው ነገር ሳይሆን ሳይንሳዊ ምርምር የሚጠይቅ ነው›› ያሉት አሸብር (ዶ/ር)፤ ማዕድኑ የትኛው አካባቢ ላይ ይገኛል፤ ምን ያህል አቅም አለው የሚለው እርግጠኛ መሆን አይቻልም፤ በሳይንሳዊ ምርምር ግን ወርቅ ሊገኝበት የሚችል ቦታ ማመላከት ይቻላል። አዋጭነቱን በተመለከተ ግን ሌላ ጥናት የሚጠይቅ በመሆኑ በዘርፉ ለመሠማራት የሚፈልገው ባለሀብት አዋጭነቱን አጥንቶ ማዕድን ወደ ማውጣት ለመግባት ሁኔታዎችን ቀለል ያደርጋል።

ማዕድን መኖሩ ካልታወቀ ማዕድን የማውጣቱ ሥራ አደጋ ያለውና ማዕድን ሊገኝም ላይገኝም ይችላል። ነገር ግን መጀመሪያው መንግሥት አጥንቶ አመላካች ቦታውን ካሳየ ባለሀብቱ ደግሞ ማዕድን አላቸው ተብለው የተለዩ ቦታዎች ላይ ኢንቨስት ማድረግ ይችላል። ይህም አደጋውን የሚቀንስ ይሆናል። ያም ሆኖ ማዕድን ማውጣት ከፍተኛ የኢንቨስትመንት አቅምን ይጠይቃል ሲሉ አብራርተዋል።

‹‹በተለይ ማዕድን ማውጣት ላይ መሠረታዊ የሆነ ጂኦሎጂካል ካርታ ካለ ማዕድን ያለበትን ቦታ መለየት ይቻላል። በክልሉ አቅም የተለዩ ቦታዎች በአብዛኛው ትኩረት ተሠጥቷቸው የተሠሩ ሲሆን በዚህ መሰረት አመላካች ጂኦሎጂካል ካርታ መሥራት ተችሏል›› ብለዋል።

ዩኒቨርሲቲው በራሱ በጀት በሚያሠራው የማዕድን ጥናት አማካኝነት በወሎ የማንጋኒዝ እና ቡሬ የወርቅ ማዕድናት ላይ ጥናት ያደረገ ሲሆን የጥናቱም ውጤት ለክልሉ ማዕድን ቢሮ መስጠቱን አመላክተዋል። ‹‹ከማዕድን ቢሮ ጋር የተሻለ ግንኙነት ስላለን ብዙ ሥራዎች አብረን እየሠራን ነው። ለአብነትም በነዳጅ ማዕድን ወሎ ወረኢሉ አካባቢ ጥናት የተካሄደ ሲሆን የተገኘው ውጤት ገለጻ ተደርጎል። ዩኒቨርሲቲው እንደዚህ አይነት ተያያዥነት ያላቸው ፕሮጀክቶችን በመሥራት ለቢሮ እያቀረበ ይገኛል›› ሲሉ አስረድተዋል።

እንደ እሳቸው ማብራሪያ፤ በአሁኑ ወቅት ደግሞ ከማዕድን ቢሮ በተደረገ ስምምነት መሠረታዊ የጂኦሎጂካል ካርታ እየተሠራ ነው። የአለቱን አይነት፣ ስርጭት እና ሁኔታን በማጥናት በዚህ መነሻነት ደግሞ በክልሉ ምን አይነት ማዕድናት ሊገኙ ይችላሉ የሚለውን ጭምር አመላካች ካርታ ይሠራል። ይህ ሥራ ለአንድ ዓመት ያህል የሚቆይ ሲሆን፤ ሥራው በየጊዜው የተለያዩ ሂደቶች መሻገር ይጠበቅበታል። አሁን ላይ በቅድሚያ የሳተላይት ምስሎች፣ ከዚህ ቀደም ከተሠሩ ሥራዎችና ከኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ በመውሰድ ይሠራሉ። በመቀጠልም የመጀመሪያ ዳሰሳ ስራ የሚሰራ ሲሆን፤ ከዚያም በእቅዱ መሰረት በጥልቀት ያለውን ጂኦሎጂካል ካርታ ሥራ ይሠራል። በዚህ ሂደት የተገኘው ናሙና ሀገር ውስጥ የሚሠራውን ሀገር ውስጥ እንዲሠራ፤ ውጭ ሀገር የሚላከውን ወደ ውጭ አገር በመላክ ትንተናው ተሠርቶ ካለቀ በኋላ ሪፖርት በማድረግ ካርታው የሚሠራ ይሆናል።

እስካሁን የተሠራው አብዛኛው ሥራ የጂኦሎጂካል ካርታ ነው፤ በማዕድን ፍለጋ ዙሪያ የተወሰኑ ሥራዎች መሠራታቸውን አመላክተዋል። የማዕድን ጥናት የተለያየ ሂደት ስላለው ማዕድኑ ወዳለበት አካባቢን እያጠበቡ አለኝታ ወደሆነበት አካባቢ መሄድን የሚጠይቅ እንደሆነ ይገልጻሉ። ‹‹ይህም በዞኑ የወርቅ ማዕድን አለ ካልን፤ ያን የወርቅ ክምችቱ ምን ያህል ነው የሚለውንም ማየት ይቻላል›› ብለዋል።

‹‹በማንኛውም አለት ውስጥ መጠኑ በጣም ጥቂት ሊሆን ይችላል እንጂ ወርቅ አለ›› የሚሉት አሸብር (ዶ/ር)፤ ‹‹አንድን ድንጋይ ተፈጭቶ ሂደቶችን አልፎ አዋጭ የሚሆነው እንደ ገበያው የወርቅ ዋጋ ቢለያይም በአንድ ቶን አለት ውስጥ 1 ነጥብ 5 ግራም ወርቅ ካለ አዋጭ ነው ማለት ነው። ከዚህ በታች ከሆነ ያንን ወርቅ ለማውጣት የሚደረገው ጥረት አዋጭ ላይሆን ይችላል›› ሲሉ አስገንዝበዋል።

የዳሰሳ ጥናት በተደረገባቸው አካባቢዎች የማዕድን አለኝታነትና ያለውን አቅም በመለየት አመላካቾች የተጠቆሙበት ሁኔታ መኖሩን ይገልጻሉ። ለምሳሌ ወንበርማ አካባቢ በተደረገው ጥናት ወርቅ መኖሩን አመላካቾች ተገኝተዋል። ነገር ግን ምን ያህል የወርቅ ክምችት በምን ያህል ርቀት የሚለውን ለማወቅ ጥልቀት ያለው ጥናት ማድረግን ይጠይቃል። በተለይ ውድ ለሆነ እንደ ወርቅ አይነት ማዕድናት ላይ ጥልቅ ጥናት ሳይደረግ እንደዚህ አይነት ክምችት አለን ማለት እንደማይቻል አስታውቀዋል።

የጂኦሎጂካል ካርታ መሠራቱ ዋና ዓላማ ክልሉ ላይ በማዕድን ዘርፍ ለመሠማራት የሚፈልግ ባለሀብት ሲመጣ የትቦታ ላይ ኢንቨስት ማድረግ እንደሚችል ለማመላከት ታስቦ ነው። ያሉት አሸብር (ዶ/ር)፤ ማዕድኑ የት ቦታ ላይ በተሻለ መልኩ ይገኛል የሚለው በሚያጠና እንደመሆኑ ጂኦሎጂካል ካርታው መሥራቱ ለክልሉ የሚሰጠው ጠቀሜታ ብዙ እንደሆነ ይናገራሉ። ሥራው ሲያልቅ ክልሉ ማዕድን አመላካች ካርታ ይኖረዋል ማለት ስለሆነ አንድ ባለሀብት የብረት ማዕድን ላይ ኢንቨስት ማድረግ እፈልጋለሁ ብሎ ቢመጣ ክልሉ የብረት ማዕድን ያለበት አካባቢ በቀላሉ በመጠቆም ባለሀብቱ ቦታው ላይ በመሄድ ጥልቅ ጥናት እንዲያደርግና አዋጭ ከሆነ እንዲሠማራበት ለማድረግ ያስችለዋል። ነገር ግን እንደዚህ አይነት ጥናቶች ከሌሉ ባለሀብቱ የት ቦታ ላይ ኢንቨስት እንደሚያደርግ ስለማያወቅ ተግዳሮት ይሆንበታል ብለዋል።

**በፍኖተ ካርታ የእውቀት ክፍተት አንዱ ተግዳሮት እንደሆነ ተመላክቷል። የእውቀት ክፍተቱን ለመሙላት በክልሉ ማዕድን ቢሮ ያሉትን ባለሙያዎች ከዩኒቨርሲቲ ጋር በማቀናጀት ልምድና እውቀት እንዲያገኙ፣ የተሠራው ሥራም በቀላሉ እንዲረዱትና እንዲተነትኑ ለማድረግ ጥረት እየተደረገ ነው**

ቀደም ሲል በተሠራው ፍኖተ ካርታ እንደተመላከተው የክልሉን ማዕድን ለማወቅ የክልሉ መሠረታዊ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ አለመሥራት እንደተግዳሮት ተወስዷል። ያሉት አሸብር (ዶክተር)፤ በክልሉ ማዕድን አመላካች ለመሥራት የተሞከረ ሙከራ ቢኖርም እንኳን በደንብ ተቀናብሮ በጥናት ተደግፍ የተሠራ የክልሉ ማዕድን አመላካች ካርታ የለም። በመሆኑም ጂኦሎጂካል ካርታ መሠራቱ በዋነኛነት ይህን ክፍተት ለመሙላት ያስችላል። ሌላኛው የመዋቅር ችግር እንደነበር የተመላከተ ሲሆን፤ አሁን ላይ በተወሰነ መልኩ የተፈታበት ሁኔታ መኖሩን ይገልጻሉ።

በፍኖተ ካርታ የእውቀት ክፍተት አንዱ ተግዳሮት እንደሆነ ተመላክቷል። የእውቀት ክፍተቱን ለመሙላት በክልሉ ማዕድን ቢሮ ያሉትን ባለሙያዎች ከዩኒቨርሲቲ ጋር በማቀናጀት ልምድና እውቀት እንዲያገኙ፣ የተሠራው ሥራም በቀላሉ እንዲረዱትና እንዲተነትኑ ለማድረግ ጥረት እየተደረገ ነው። በተጨማሪ የአቅም ችግር ለመቅረፍ የአጭር ጊዜ ሥልጠናዎች እና የእውቀት ሽግግር እንደሚያደርጉ ተናግረዋል።

የማዕድን ዘርፉ ዋነኛ ዓላማ ያሉትን የማዕድን ሀብቶች ተጠቅሞ የክልሉን ሕዝብ ከድህነት ማላቀቅ ነው ያሉት አሸብር (ዶ/ር)፤ ይህም በክልሉ በማዕድን ዘርፍ ኢንቨስት ማድረግ የሚፈልግ ባለሀብት በጥናት የተደገፈ መረጃ እንዲያገኝ እድሉ መፍጠር ነው። ‹‹በአጠቃላይ ክልሉንም ሆነ ሀገር ሊያሳድግ የሚችል ኢንቨስትመንት ሲመጣ የተሟላ ሳይንሳዊ የሆነ መረጃ ማቅረብ አለብን›› ሲሉ አስገንዝበዋል።

እሳቸው እንደሚሉት፤ ለማንኛውም የማዕድን ኢንቨስትመንት መሠረታዊ ጂኦሎጂካል ካርታ መሥራት ያስፈልጋል። ጂኦሎጂካል ካርታ ካለ ባለሀብቱ ወደ ቀጣይ ሂደት በቀላሉ ሊሄድ ይችላል። እንደክልል ያለው የማዕድን ሀብት ለማወቅ ጥናት በማጥናት ስለሚያስፈልግ ዩኒቨርሲቲውም ባሉት ባለሙያዎች በመታገዝ ኃላፊነት ወስዶ የክልሉ የማዕድን ሀብት እንዲለማ የሚያስችሉ ሥራዎች እየሠራ ነው።

ማዕድን እንደሀገር ትኩረት የተሰጠው ዘርፍ በመሆኑም በክልሉ አሁን ላይ ጥሩ ጅማሮዎች አሉ የሚሉት አሸብር (ዶ/ር)፤ ዩኒቨርሲቲው በጥናት ሆነ በሳይንሳዊ ትንታኔም ያሉ ክፍተቶችን በመሙላት በማዕድን ኢንቨስትመንት ባዶ የነበረው መረጃ እያሟላ መሆኑን ያመላክታሉ። ‹‹ማዕድን በአንዴ ተሰርቶ የሚያልቅ ባለመሆኑ በሂደት የክልሉን ሙሉ መሠረታዊ የሆነ የጂኦሎጂካል ካርታ እና የማዕድን አለኝታ ኖሮ ለማዕድን የተመቻቸ አካባቢያዊ እንፈጥራለን›› ሲሉ ተናግረዋል።

ዩኒቨርሲቲው የአካዳሚክና የምርምር ተቋማት እንደመሆኑ በላብራቶሪ በኩል ያለውን ክፍተት በመሙላት ለመደገፍ ባለፉት አራት ዓመታት ከ40 እስከ 50 ሚሊዮን ብር በላይ የሚያወጡ ላብራቶሪ ማሽኖች ገዝቶ መትከል ችሏል። በቀጣይ መሠረታዊ የሚባሉትን አስፈላጊ ቁሳቁሶች እያሟላ ለማዕድን ዘርፉ መፍትሔ መስጠቱን ይቀጥላል። የክልሉ ማዕድን ሀብት በማልማት ረገድ በላብራቶሪና በጥናት ድጋፍ እያደረገ ነው።

በተጨማሪም የአጭርና የረጅም ጊዜ ሥልጠናዎች በማዘጋጀት ለባለሙያዎች ይሰጣል። እንዲሁም በአካዳሚክ ትምህርት የመጀመሪያ ዲግሪ የጂኦሎጂ ትምህርት ዘርፍ የሚሰጥ ቢሆንም ትምህርቱ ማዕድን፣ የከርሰምድር ውሃው፣ አካባቢ እና ኢንጂነሪግ ያካተተ ጠቅለል ያለ ትምህርት የሚሰጥበት ነው። በቅርቡም ሁለተኛ ዲግሪ (በማስተር ደረጃ) በማሳደግ ኢኮኖሚክ ጂኦሎጂ ዘርፍ (በሚኒራል ዲፖዚት) ዘርፍ ትምህርት እንዲሰጥ ተደርጓል። ይህም በዘርፉ የሠለጠነና ብቁ የሰው ኃይል ለማፍራት ያስችላል።

‹‹በማዕድን ዘርፉ የሚሠሩ ሥራዎች ከዩኒቨርሲቲው ዓላማ ጋር አብሮ የሚሄዱና በክልሉ የማዕድን ቢሮ ተቀባይነት ያላቸው ናቸው። እኛም እንደዩኒቨርሲቲ በምንሠራው ሥራ የሚቀበለን ስላለ ደስተኞች ነን። በእውቀትና ክህሎት፣ በአጭርና ረጅም ሥልጠናዎች እና ጥናት እና በላብራቶሪ በኩል ድጋፍ በማድረግ አገልግሎት እየሠጠን ነው›› ሲሉ አስገንዝበዋል

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## ትንሽ ብቻ ዞር...

**ቴልጌልቴልፌልሶር (የኩሽ አሽክታብ)**

ማንበብ ስወድ ለጉድ ነው። ከዕለት ተዕለት ሱሶቼ መሐል በኩሩ ሆኖ እንደቡናና ትንባሆ ያዳክረኛል። የእውቀት ማረፊያው አእምሮ ነው። በልብ በኩል ደግሞ ስር ይሰዳል። የአእምሮ ብቻ መሆንና የአእምሮና ልብ መሆን የተለያዩ ማንነቶች ናቸው። የአእምሮ ብቻ መሆን እንደአሜሪካና ሰሜን ኮርያ እየተዛዛቱ መኖር ሲሆን፤ የአእምሮና ልብ መሆን ግን ከዛ የገዘፈ ነው።

ይህንን ከሚያክል ፍልስፍና ጋር እየተሟገትኩ ወዳንድ ካፌ ሰተት አልኩ። ቡና አዘዝኩ። በስኳር ብያት በጨው፣ በጤናዳም ብያት በሌጣው፣ ለዛውም በሽራፋና በገባጣ ስኒ፤ ይሄ ሳያንስ ግማሹን ሳህኑ ላይ አፍስሳ ድርበብ የሆነ ቡና አቀረበችልኝ። እስኪ ይሁን ስል ወደ አፌ አስጠጋሁት። ቡናው ቀዝቅዞ ነበር። አንዳንድ ቀኖችን እንዲህ ናቸው የሆነ ቦታ፣ የሆነ ሰው ላይ ይጥሉንና ያጎድሉናል።

በዚህ ስሜት ውስጥ ሳለሁ ሎተሪ አዟሪና ጋዜጣ ሻጭ፣ እኔ እበልጥ እኔ በሚመስል የብኩርና ፉክክር ይመስለኛል፤ ሰፊውን በር ለአንደኛነት ተቀራምተውት እኩል በሚባል ፍጥነት ወደ ውስጥ ተማገዱ። ከሁለቱም ከንፈር በላይ የንፍጥ ድርቆሽ ይታያል።

ለሃያ አመት ሎተሪ ቆርጬ ከማስተዛዘኛ ባለፈ ዕድል ያልቀናኝ ባተሌ ነኝ። ለዛሬ ግን ሎተሪውን አልደፈርኩም። ወደ ጋዜጣው ዞሬ ባለላባሙን አፍንጫ ልጅ በምልክት ጠራሁት። አፌ የነበረውን ስኒ ወደ ጠረጴዛው ልመልስ አፍታ በወሰድኩበት ቅጽበት እንዴት እንደደረሰ እንጃ፣ ጎኔን ሲታከክ አገኘሁት። ምንም አላልኩ። የራሴን ልጅነት ከእሱ ልጅነት ጋር በላመሉ አነካክቼ ወደ ታቀፈው የጋዜጣ ክምር ተላለፍኩ። ተራችን እስኪደርስ ድረስ አቃቂር አውጪዎች ነን፤ ተራችን ሲደርስ አቃቂሩ በእኛ ላይ ነው።

ጋዜጣውን መዝገቤ ፊት ለፊቴ ዘረጋሁት። ሰከን ብዬ ፍሬ ሀሳቡን ለመረዳት ሞከርኩ። በትምህርት ዘርፉ ላይ የተጻፈ መረጃ ተኮር ጥናታዊ ጽሑፍ ሆኖ አገኘሁት። በአንድ ሁነኛ ሊቅ የተጻፈ መሆኑ ደግሞ ይበልጥ እንድመሰጥበት አደረገኝ። የእኛን ሀገር መነካካቱ፣ ከቴክኒክና ሙያ ይልቅ ዩኒቨርሲቲ ተኮር ትውልድ መፈጠሩን በመተቸት ያወሳል። አንዳች እንዳያመልጠኝ አይኖቼን ወደ ጽሑፉ መግቢያ በመስደድ ጀመርኩ።

ከንባቤ በኋላ ጋዜጣውን ዘግቼ ስለሀገሬ መብሰልሰል ጀመርኩ። ልቤ መንደራችን ወዳለው ለብዙ ሥራ አጥ ወጣት የሥራ ዕድል ወደ ፈጠረው ወዳጄ ሸፈተ። በሥራና በክሂሎት ከራሳቸው አልፈው ለሌሎች ወደ ተረፉ፤ ከመንግሥት እጅ ሽልማት እስከመቀበል ወደ ደረሱ ጓደኞቼም ተዛመትኩ። ራሴን ሸፍኜ እንጂ ቴክኒክና ሙያ ተምረው ከተሳካላቸው መሐል አንዱን ነኝ። የእኔ ይቆይና ስለሁለቱ ወዳጆቼ ላውጋችሁ።

የብዙዎቻችን ሕልም ፕሪፓራቶሪ መግባት፤ ከዛም ዩኒቨርሲቲ ሰንብቶ መመረቅ ስለነበር፤ አጋጣሚ ሆኖ እኔና አራት ጓደኞቼ ቴክኒክና ሙያ ገባን። ያን ጊዜ ሳስበው በብዙ ኀዘን ነው። ሕይወት ቀጠለ..እየመረረንም ቢሆን በእንጨት ሥራ፣ በሥራ ፈጠራ ክሂሎት እና በኤሌክትሪክ ዝርጋታ ላይ ሰንብተን ተመረቅን። ነገሮች ሁሉ ባልጠበቅነው መንገድ መሄድ ጀመሩ። ጊዜው የእኛ የሆነ እስኪመስለን ድረስ የታጠፍንባትን ያቺን የሕይወት እጥፋት እያሰብን ጮቤ ረገጥን። አብረውን የገቡ ሰባት ልጆች በላቀ ውጤት እዛ ሲቀሩ እኔና ወዳጆቼ ግን በሙያችን የግል ሥራችንን ለማስቀጠል ወጣን። አንደኛው በተማረው የእንጨት ሥራ መዲናችን ላይ ስመጥር ቢሊየነር ሆኗል። ከሀገር አልፎ ከዱባይ በሚያስመጣቸው ዘመናዊ ፈርኒቸሮቹ ለብዙዎች የእንጀራ ገመድ በመሆን ስሙን በወርቅ ቀለም ጽፏል። ሁለቱ በተማሩበት የልብስ ስፌት ሙያ ሰፊ የገበያ አማራጮችን በመዘርጋት ከታማኝ ግብር ከፋዮች ተርታ ተሰልፈዋል። እኔም በተመረቅሁበት የኤሌክትሪክ ዝርጋታ ስራ ትላልቅ ሆቴሎችንና ሕንጻዎችን በጨረታ በመውሰድ ለብዙዎች ተርፌአለሁ። በጣም የሚገርመው ዛሬ ለበርካታ የዩኒቨርሲቲ ምሩቃን የሥራ እድሎች ሆነናል፤ በርካቶችንም ቀጥረን አብረውን በመሥራት ላይ ናቸው።

አሁን ላይ ለትውልዱ የማስተላልፈው፣ ትውልዱ ቢያውቀው የምላቸው ሁለት ነገሮች አሉ። የመጀመሪያው አእምሯችንን በእውቀት እንደምናፋፋ ሁሉ እጆቻቸውን በሥራ የምናፍታታበትን የሙያ መቅሰሚያ ኢንስቲትዩት መድፈር..ሌላው ከዩኒቨርሲቲ አስተሳሰብ ወጥተን ሕይወት በከፈተችልን መንገድ ስኬታማና ውጤታማ በመሆን ከባላሻራዎች ጎን መቆም የሚሉት ናቸው።

ሰፊ ሀገር..ግዙፍ ታሪክ በብዙኃነት የታጨቀ እሴትና ባሕል ዋነኛ መጠሪያችን ነው። በሥርዓት የዳበረ፣ በወንድማማችነት የቆነጀ ከዚህ እስከዛ የሌለው የኅብረብሔራዊነት ውሕድ ሌላኛው ቅጥያ ስማችን ነው። በዚህ ደማቅ ስም ውስጥ ድህነትን ጠሪ፣ ኋላቀርነትን ዘካሪ ሀሳብና ብስለት ያልተቃኘባቸው ማኅበራዊ ልምምዶች ውበታችንን አጠይመውታል። እነዚህ ልምምዶች ሀሳብ የገዘፈበትን ልዕለሰብ ሽረው ለድህነት በር ከፋች ሆነው አብረውን ከሰነበቱ ከራርመዋል። እንደመነሻ የዩኒቨርሲቲና የቴክኒክና ሙያ ተሞክሮዎቻችንን ቃኘን እንጂ ከመማር ማስተማሩ ጋር በተያያዘ የውጤት ማሽቆልቆልንና ስንፍናን ከሙያ ሥልጠናና ከተግባረዕድ ጋር የማያያዝ ችግሮች አሉብን።

ከዚህ ሁሉ የሀሳብ ንውዘት ወጥቼ ወደ ራሴ ስመለስ.. አይ የኔ ነገር! ያን ባለላባም አፍንጫ ጋዜጣ ሻጪ ሂሳብ አልከፈልኩት ኖሮ ፊቴ እንደተገተረ አገኘሁት። በእውነቱ ጸጸተኝ። ልክ እንዳይደለሁ ከመሰማት ባለፈ የጥፋተኛነት ለበቅ ሸነቆጠኝ። ስንት ደቂቃ ዝም አልኩ? ለምን ያክል ጊዜ አርምሞ ውስጥ ነበርኩ? በዛ ሁሉ ዝምታ ውስጥ አብሮኝ ዝም እንዳለ ሳስብ፣ ለሆሳሴን ሳይገረስስ ወደራሴ እስክመለስ መጠበቁን ሳስብ፣ ከዓላማው አስተጓጉዬ ስሬ እንደገተርኩት ሲገባኝ በራሴ አፈርኩ። አይኔን አተራምሼ ንፍጣሙን ጓደኛውን ሻትኩት .. አልነበረም። ጓደኛው ትቶት እንደሄደ ሳውቅ ደግሞ የበለጠ በዳይ መሆኔ ተገለጠልኝ። አንዳንድ ከነፍስ ማጥፋት እኩል የማይተናነሱ ይሄን መሳይ ጥፋቶች በእያንዳንዳችን እጅ ላይ አሉ። ለእኛ ምንም የማይመስሉን ሌላው ጋ ግን እንደፓስፊክ የገዘፉ ባዶነቶች።

እንደእኔ ያሉ በቴክኒክና ሙያ በልጽገው ራሳቸውን የቀየሩ አእምሮዎች ሕይወትን በተመለከተ ከጊዜ ጋር የሚያቆራኙት መልስ አላቸው። ደፍሮ አይናገረኝ ወይም አይክሰሰኝ እንጂ ከዚህ ብላቴና ላይ ብዙ እንዳጎደልኩ አውቃለው። ሕይወት ለእኔ ጊዜና ስኬት የተሰሉበት እውቀት፤ አሊያም አረዳድ፤ አሊያም ፍልስፍና ወይም ተሞክሮ ነው። የቆመበትን በማስላት ከዋጋው በለጥ አድርጌ በመክፈል ልክሰው እና ቀን ሙሉ ላስፈነድቀው አሰብኩ። ከዚህ ውጪ ምንም መካሻ እንደሌለኝ ሳውቅ ና ወደዚህ ስል በአይኔ ጋብዤው ከፒጃማዬ ውስጥ መዝገቤ እጁ ላይ አስጨበጥኩት። አምጣ የምለው መስሎት ባለማመን እስከ ውጪ በር ድረስ የኋሊት እየተራመደ ሲያየኝ ነበር። የውጪውን በር እንዳለፈ በሳቀ ፊት እንዴት ፈጥኖ እንደሮጠ ለሁልጊዜ ይገርመኛል። ሩቅ ደርሶ ዞሮ ሲያየኝ በበሩ በኩል ሳስተውለው ነበር። መጨረሻው ናፍቆኝ ከተቀመጥኩበት ተነስቼ ቃኘሁት ... ልጃገረድ ነፍሱ ራሷን በፀደይ ሰማይ ስር ደብቃ እንደመብረቅ ስትብለጨለጭ አየኋት። ጸጸቴ ድራሽ አባቱ ጠፋ . . አንድ እኩል ሆንን።

መጥፎ ልምምዶቻችንን ሽረን እጆቻችንን ሙያ ማስለመድ ከነበርንበት ፈቀቅ የምንልበት የቀጣዩ ጊዜ ትንሳኤአችን ነው› በሚል መቋጫ ሀሳብ ለዛ መራራ ቡና 25 ብሬን ገብሬ ወደ ቤቴ ተመለስኩ። ባለላባሙ አፍንጫ ጋዜጣ ሻጪ በሄደበት መንገድ ዓይኔን ስሰድ ከርቀት አየሁት ... ብርሀን ለብሶ።

# ዓለም አቀፍ

## የስዊድኗ ከተማ ነዋሪዎችን ለመሳብ መሬት በ10 ሳንቲም አቀረበች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

በነዋሪዎች ድርቅ የተመታችው የስዊድኗ ጎተን ከተማ ቤት መሥሪያ መሬት በርካሽ አቀረበች፡፡

የስዊድኗ ጎተን ከተማ በአውሮፓ ካሉ ከተሞች መካከል በየዓመቱ አነስተኛ ሕጻናት ከሚወለዱባቸው ከተሞች መካከል አንዷ ናት፡፡

እንዲሁም ይህች ከተማ በእድሜ የገፉ ሰዎች ከሚኖሩባት ከተሞች መካከልም አንዷ ስትሆን የከተማዋ አስተዳደር ተጨማሪ ነዋሪዎች እንዲመጡ ማበረታቻዎችን ዘርግቷል፡፡


ለሁለት ዓመት ይቆያል የተባለው ይህ ማበረታቻ ሕጋዊ የመኖሪያ ፈቃድ ያላቸው ሰዎች ሁሉ በጎተን ከተማ የመኖሪያ ቤት መሥሪያ ቦታ በርካሽ አቅርቧል።

የከተማዋ ከንቲባ ጆሃን ማንሰን ለዩሮ ኒውስ እንዳሉት ወደ ጎተን ከተማ መጥተው ለሚኖሩ እና ቤት መሥሪያ ለሚፈልጉ ሰዎች አንድ ስኩዌር ሜትር ቦታ በአንድ የስዊድን ክሮና ወይም በ0 ነጥብ 08 ዶላር ዋጋ እንሸጣለን ብለዋል፡፡

ይህ ማበረታቻ ከተያዘው 2024 ጀምሮ እስከ ቀጣዩ ዓመት ድረስ ይቆያል ያሉት ከንቲባው ለሽያጭ የቀረበው ቦታ ለመኖሪያ ምቹ በሆኑ በከተማዋ እምብርት ላይ የሚገኝ እንደሆነም ተናግረዋል፡፡

“ለማንኛውም ሰው መሬቱን ለመሸጥ ዝግጁ ነው ዋናው እዚህ እኛ ከተማ መጥቶ ለመኖር ፍላጎት ብቻ ይኑረው” ሲሉም ከንቲባው አክለዋል፡፡

ይሁንና መሬቱን የገዙ ነዋሪዎች በሁለት ዓመት ውስጥ መኖሪያ ቤቱን መገንባት አልያም ግንባታውን መጀመር እንደሚኖርባቸው ይህ ካልሆነ ግን መሬቱን ሊነጠቁ እንደሚችሉ በዘገባው ላይ ተጠቅሷል፡፡



ጎተን ከተማ በአውሮፓ ካሉ ውብ ስፍራዎች መካከል አንዷ ስትሆን በመልክዓ ምድር አቀማመጥ፣ የዱር እንስሳት እና ሌሎች የሚጎበኙ ስፍራዎችን የያዘች ከተማ ናት፡፡

ከተማዋ ማስታወቂያውን ካወጣች በኋላ በአንድ ወር ውስጥ ሦስት የመኖሪያ ቤት መሬት የተሸጠ ሲሆን በቀጣዮቹ ጊዜያት ተጨማሪ ገዢዎች እንደሚመጡ ይጠበቃል፡፡

## እሥራኤልና ሊባኖስ ወደከፋ ጦርነት እንዳያመሩ አስግቷል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

እሥራኤልና ሊባኖስ የገቡበት ፍጥጫ ወደከፋ ጦርነት እንዳያመራ አስግቷል።

በአሜሪካ ጉብኝት እያደረጉ የሚገኙት የእሥራኤል መከላከያ ሚኒስትር ዮቭ ጋላንት እሥራኤል ከሊባኖስ ጋር ጦርነት ውስጥ መግባት እንደማትፈልግ ተናግረዋል።

“ጦርነቱን አንፈልገውም፤ ይሁን እንጂ በማንኛውም መንገድ ምላሽ ለመስጠት ዝግጁ ነን፤ ሄዝቦላህም ጦርነቱ ቢጀመር በሊባኖስ ላይ የሚደርሰውን ከባድ ኪሳራ ጠንቅቆ ያውቀዋል” ነው ያሉት።

የአሜሪካ መከላከያ ሚኒስትር ዮቭ ጋላንት በበኩላቸው ከሄዝቦላህ ጋር የሚደረግ ጦርነት



በመካከለኛው ምሥራቅ ከባድ ቀውስ እንደሚያስከትል ነው ለጋላንት የነገሯቸው።

በጋዛው ጦርነት የእስራኤል ሁነኛ አጋር መሆኗን ያሳየችው አሜሪካ የሊባኖስ እና እሥራኤል ውጥረት በዲፕሎማሲያዊ ንግግር እንዲፈታ ጥሪ ማቅረቧንም ፍራንስ 24 አስነብቧል።

ጀርመን እና ካናዳ በሊባኖስ የሚኖሩ ዜጎቻቸውን ሀገሪቱን ለቀው እንዲወጡ የመከሩ ሲሆን፥ ውጥረቱን የሚያረግብ ንግግር እንዲጀመር ጠይቀዋል።

የመንግሥታቱ ድርጅት የሰብዓዊ ድጋፍ አስተባባሪ ማርቲን ግሪፍትስ ከጄኔቫ በሰጡት መግለጫ ሊባኖስ ላይ የሚጀመር ጦርነት ወደ ሶሪያና ሌሎች ሀገራት ሊስፋፋ እንደሚችል አስጠንቅቀዋል።

የሊባኖስ ብሔራዊ የዜና ወኪል እስራኤል በአንድ ቀን ብቻ 10 የአየር ጥቃቶችን መፈጸሟን ዘግቧል።

ሄዝቦላህ በአንጻሩ በእሥራኤል የድንበር ከተሞች በሚገኙ ወታደራዊ ጣቢያዎች ላይ በ24 ሰዓት ውስጥ ስድስት ጥቃቶችን መፈጸሙን ነው ያስታወቀው።

የቡድኑ መሪ ሐሰን ናስራላህ ባለፈው ሳምንት በሰጡት መግለጫ እሥራኤል በሊባኖስ ላይ ጦርነት ብታውጅ የሚደርስባትን ታውቀዋለች ሲሉ መዛታቸው ይታወሳል።

ናስራላህ “ጠላቶቻችን (እሥራኤል) ለከባድ ጊዜ በሚመጥን ደረጃ ያደረግነውን ዝግጅት ያውቁታል፤ የድሮን እና ሮኬት ጥቃቶችን ሊቋቋሙት አይችሉም” ነበር ያሉት።

የእሥራኤል ጠቅላይ ሚኒስትር ቤንያሚን ኔታንያሁ በጋዛ “መጠነ ሰፊው ዘመቻ” እየቀነሰ መሄዱን ካሳወቁ በኋላ 10ኛ ወሩን ሊይዝ የተቃረበው ጦርነት መቀዛቀዙ እየተነገረ ነው።


እሥራኤል ከጋዛ የምታስወጣቸውን ወታደሮቿን ወደ ሊባኖስ ድንበር እንደምታሰማራ ኔታንያሁ መናገራቸውም ይታወሳል።

ማህበራዊ

# ሀገርኛ

# ስብዙዎች እፎይታ እየሰጠ ያለው ማዕከል

**ሰሚራ በርሀ**




የኢትዮጵያ የልብ ህሙማን ህጻናት መርጃ ማዕከል በልብ ህመም ለሚሰቃዩና ህክምና ለሚያስፈልጋቸው ዜጎች ያለምንም ክፍያ በነጻ ህክምና የሚሰጥ ብቸኛው ተቋም ነው። ማዕከሉ ይህንን በጎ ተግባር ከሶስት አስርት ዓመታት በላይ ሲያከናውን ቆይቷል። የማዕከሉ መስራች ዶክተር በላይ አበጋዝ፤ በወቅቱ ‹‹አንድ ብር ለአንድ ልብ›› በሚል ሃሳብ ብዙ ኢትዮጵያውያንን ተሳታፊ ማድረግ እንደቻሉ አይዘነጋም።

ይህ በቅን ልቦች ጠንሳሽነት የተጀመረው በጎ ሥራ ከእያንዳንዱ ሰው ደርሶ ሃሳቡ ፍሬ እንዲያፈራ ብዙ ጥረት ተደርጓል። በተለይም ማህረሰቡን ተሳታፊ ለማድረግ መረጃውን በማሰራጨት በኩል 100 የሚጠጉ በጎ ፍቃደኞች፣ የማህበረሰብ አንቂዎች፣ የኪነጥበብ ባለሙያዎች በብዙ ተሳትፈዋል። የመገናኛ ብዙኃን በበኩላቸው ማዕከሉን በመደገፍ ረገድ የነበራቸው ሚና ቀላል ግምት የሚሰጠው አልነበረም። በዚህም በርካታ ታማሚ ልቦች እፎይታን ማግኘት ችለዋል።

አቶ ሙሳ ቃሲም የማዕከሉን አገልግሎት ፈልገው ከመጡ ታካሚዎች መካከል አንዱ ነው። አቶ ሙሳ፤ ልጁን ለማሳከም ከአርሲ ዞን መርተሪ ወረዳ አቦምሳ ከምትባል ወረዳ የመጣ ሲሆን፤ ልጁ የልብ ህመም እንዳለባት ያወቀው የአራት ዓመት ልጅ እያለች ነበር ከዚያም ባደረገችው ምርመራ ወደ ናዝሬት ለተሻለ ህክምና ተላከች። በተደረገላት ምርመራ የልብ ህመም እንዳለባት ማወቅ ችለዋል።

ወደ ማዕከሉ ከመጡ ሰባት ዓመታትን ማስቆጠራቸውን የሚናገሩት አባት አንድ ወቅት ወረፋቸው ደርሶ ነገር ግን ልጃቸው ጉንፋን በመታመሟ ምክንያት ሳትታከም ቀርታለች። ህክምና ለማግኘት ለዓመታት ወደ ማዕከሉ የተመላለሱት አቶ ሙሳ ያለውን ወረፋ ሲገልጹ ‹‹የምመጣው ከሩቅ ሀገር ነው 180 ኪሎ ሜትር ይሆናል። አሁን ከመጣሁ 15 ቀን ሆኖኛል ግን ምኖረው ለልጄ ስለሆነ እመላለሳለሁ›› በማለት ነው። በማዕከሉ አገልግሎቱን ማግኘት ከጀመሩ በኋላ ያለውን ጠቀሜታ ሲገልጹም ‹‹የልብ በሽታ እኔ በምኖርበት ቦታ ብዙም አይታወቅም እኔም የምትድን አልመሰለኝም እዚ ስመጣ ያገኘሁት መረጃ በጣም ጥሩ ነው›› ብለዋል። በማዕከሉ የልብ ህመም እንዳለባት ታውቆ ህክምናውን ስትጀምር የአራት ዓመት ልጅ የነበረችው ሀዊ ሙሳ አሁን የ 11 ዓመት ልጅ እና የአምስተኛ ክፍል ተማሪ ሆናለች።

ሌላኛዋ ታካሚ ወይዘሮ ባንቻየሁ በለጠ ትባላለች። ባንቻየሁ የልብ ህመም እንዳለባት ያወቀችው በልጅነቷ ሲሆን፤ አሁን ላይ ትምህርቷን አጠናቃ በሥራ ላይ ትገኛለች። ወደ ማዕከሉ ከመምጣቷ በፊት እጅግ ታማ ከሀገር ውጪ ሄዳ እንድትታከም እና ከአንድ ሚሊዮን ብር በላይ ገንዘብ ለህክምናው ተጠይቃ እንደነበር ታስታውሳለች። ወደ ማዕከሉ መጥታ ክትትል ስጀምርም ከፍተኛ ወረፋ ጠብቋታል። ህመሙ ከቀን ወደቀን እየጨመረ ሲሄድ ከትዳር አጋሯ ጋር ሆነው ርዳታ ለመጠየቅ ወስነዋል። ‹‹ከውጭ ስታይ ደህና እመስላለሁ ነገር ግን በጣም ያመኛል። እናም በዚህ ሁኔታ እንዴት ርዳታ እጠይቃለሁ እያልኩ ወረፋዬ ደርሶ ተደወለልኝ›› የምትለው ባንቻየሁ ወረፋዋ ደርሶ ቀዶ ጥገናውን ካደረገች አሁን አንድ ዓመት እንደሆናትና በጥሩ ጤንነት ላይ እንደምትገኝ አጫውታናለች። በማዕከሉ ያሉ የጤና ባለሙያዎችን ለታካሚዎች በሚሰጡት ቦታና በሚያደርጉት እንክካቤም እጅግ ደስተኛ እንደሆነች ተናግራለች።

በውጭ ሀገር ለመታከም የወሰነችው ወይዘሮ ባንቻየሁ፤ ከአቅሟ በላይ የሆነ ወጪ በተጠየቀችበት ወቅት ህክምናውን በማዕከሉ ማግኘት በመቻሏ እጅግ ደስተኛ እንደነበረች ስትገልጽ፤ ‹‹ይህንን እድል ባላገኝ አሁን ላይ በሕይወት መቆየት አልችልም ነበር። ስለዚህ ህክምናው ለሁሉም መድረስ እንዲችል ሁሉም ሰው ይህንን ዓላማ መደገፍ አለበት›› በማለት ነው።

የኢትዮጵያ የልብ ህሙማን ማዕከል በሀገር ውስጥ የልብ ህክምና በነጻ የሚሰጥ ብቸኛው በመሆኑ እነዚህን መሰል ተቋማት እንዲበራከቱ እና የብዙዎችን ሕይወት

## የልብ ህመም እንዳለባት ታውቆ ህክምናውን ስትጀምር የአራት ዓመት ልጅ የነበረችው ሀዊ ሙሳ አሁን የ 11 ዓመት ልጅ እና የአምስተኛ ክፍል ተማሪ ሆናለች

ማትረፍ እንዲቻል ሁሉም ከማዕከሉ ጎን መቆም እንደሚገባ ያነሳችው ወይዘሮ ባንቻየሁ፤ ‹‹ማዕከሉን ለመደገፍ ትልቅ ገንዘብ ድጋፍ ማድረግ የማይችል ሰው የአጭር የጽሁፍ መልዕክት የአቅሙን መደገፍ ይችላል። ይህንን በማድረግም ብዙ ህጻናትን መደገፍ ይቻላል በማለት አስረድታለች።

የማዕከሉ ምክትል ዳይሬክተር ዶክተር ሜሮን ገብሩ በበኩላቸው በማዕከሉ በአሁኑ ሰዓት አራት ቀዶ ጥገና የሚያደርጉ ቀዶ ጠጋኝ ሀኪሞች እንዳሉ ገልጸው፤ አንድ የህክምና ባለሙያም በሳምንት ብቻውን አራት ቀዶ ጥገናዎችን መሥራት ቢችልም ለልብ ቆዶ ጥገና የሚያስፈልግና በቀጥታ ለልብ ታካሚ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች እንዲሁም መድሃኒቶች በሀገር ውስጥ በበቂ ሁኔታ አይገኙም። መድሃኒቶቹም በሌሎች የህክምና ተቋማት በቀላሉ የሚገኙ አይደሉም ብለዋል። በማዕከሉ ከሚሰጡ አገልግሎቶች መካከል ለውስጥ ታካሚዎች የተዘጋጀ የራሱ የመድሃኒት ክፍል ስለመኖሩ አንስተው፤ የመድሃኒት እና የግብዓት እጥረት ስለሚያጋጥም ሀኪሞች መሥራት ከሚችሉት አቅም በታች እየሠሩ እንደሆነ ተናግረዋል። አያይዘውም እነዚህን ግብዓች ማሟላት ቢቻል የበለጠ መሥራት እና ታካሚዎችን ማስተናገድ እንደሚቻል አስረድተዋል።

የመድሃኒት አቅርቦት እጥረት በሀገር ደረጃ በተለያዩ የህክምና ተቋማት እጥረት ያግጥማል። ይህንን ችግር ለመፍታትም የተለያዩ ሥራዎች የሚሠሩ ሲሆን፤ እንደ ዳይሬክተሯ ገለጻ ማዕከሉ አገልግሎቱን በሙሉ አቅሙ ለመስጠት እንቅፋት ከሆኑበት ጉዳዮች መካከል የመድሃኒት እጥረት አንዱ ነው። የመድሃኒቶቹ ዋጋ ውድ መሆንና በሌሎች የህክምና ተቋማትም እንደ ልብ አለመገኘት፤ እንዲሁም የልብ ህክምና በነጻ ከሚሰጠው ተቋም ጨምሮ የልብ ህክምና የሚሰጥባቸው ተቋማት ውስጥ በመሆናቸው አቅርቦቱም እንደ ልብ ወደ ሀገር አይገባም። በዚህም ምክንያት አንድና ሁለት መድሃኒት በማጣት የሚዘገዩ ህክምናዎች ስለመኖራቸው የገለጹት ዶክተሯ፤ መድሃኒቱን ለማግኘት ከተለያዩ ተቋማት ጋር በትብብር እየሠሩ እንደሆነ ተናግረዋል።

በህክምናው ዘርፍ የሚገኙ ባለድርሻ አካላት፣ መንግሥትና ማህበረሰቡ በጋራ በመሆን መሥራት እንዳለባቸው ያነሱት ዋና ዳይሬክተሯ፤ በሌሎች የሀገሪቱ ክፍሎች የሚገኘውን የሰው ሃይል አቅም በመጠቀም ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጋር መነጋገር አስፈለጊ እንደሆነም ተናግረዋል። እሳቸው እንዳሉት፤ አገልግሎት እንዴት መስጠት ይቻላል በሚለው ዙርያ መነጋርን ይጠይቃል። ይህ መሆኑም ህክምና ለማግኘት ከክልል የሚመጡ ዜጎች ወደ ክልል መምጣት ሳይጠበቅባቸው በሚኖሩበት ቦታ ህክምናውን በፍጥነት ማግኘት ያስችላቸዋል። ዋና ዋና የሚባሉ የልብ ችግሮች በዚያ እንዲታከሙ እና ተጨማሪ ህክምና የሚያስፈልጋቸው ሲኖሩ ደግሞ ወደ ማዕከሉ እንዲመጡ የሚደረግበትን አሠራር ወደፊት መፍጠር ያስፈልጋል።

በኢትዮጵያ የልብ ህሙማን ማዕከል ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ሕሩይ ዓሊ ‹‹ኢትዮጵያ አሁን ላላት የሕዝብ ቁጥር ይህ አንድ ሆስፒታል ብቻውን በቂ አይደለም። የልብ ቀዶ ጥገና ቀላል የማይባል ህክምና ሲሆን፤ ተቋሙ ከሚያስተናግደው ወረፋ አንጻር ታካሚዎችን ለማስተናገድ የምንቸገርበት ጊዜ አለ›› ይላሉ። በማዕከሉ ቀዶ ጥገና ከሚደረግላቸው እና ህክምና ለማግኘት ወደ ማዕከሉ ከሚመጡት ባሻገር ቅድመ ክትትልና ድህረ ክትትል የሚደረግላቸው ታካሚዎችም አሉ። ያም ሆኖ በማዕከሉ በዓመት እስከ 14 ሺህ ለሚደርሱ ሰዎች ነጻ የልብ ህክምና ክትትል የሚደረግ መሆኑን ያስረዳሉ።

በአሁኑ ሰዓት በማዕከሉ ውስጥ ሰባት ሺህ ታካሚዎች ወረፋ በመጠበቅ ላይ ይገኛሉ። አንድ የልብ ታካሚም ከሶስት እስከ አራት ዓመት ወረፋ ይጠብቃል። ‹‹የሚኖረው ወረፋ ረጅም በመሆኑ ምክንያትም የወረፋ ጊዜያቸው ሳይደርስ ሕይወታቸው የሚያልፉ ታካሚዎች አሉን ይህ በማዕከሉ የሚገኙ ሀኪሞችን ልብ የሚሰብር ነው›› በማለት የጉዳዩን አሳሳቢነት እንዲሁም ማዕከሉ የሚሰጠው አገልግሎት ከታማሚዎች ቁጥር ጋር የሚጣጣም እንዳልሆነ አስረድተዋል።

አሁን ላይ ካለው ችግር አንጻር እየተሰጠ ያለው አገልግሎት ብዙ የሚቀረው ነው። የሚሉት ዋና ሥራ አስፈጻሚው ማዕከሉ እጅግ ለተቸገሩ እና ለተጨነቁ ልጆቻቸው ለታመሙባቸው ወላጆች እይፎታ እየሰጠ ነው ብለዋል። ህክምና ለማግኘት ወደ ማዕከሉ ከሚመጡ ታካሚዎች መካከል በሳምንት ከአራት እስከ ስምንት የሚደርሱ የልብ ቀዶ ጥገናዎችን ይከናወናል። ነገር ግን ለልብ ቀዶ ጥገና የሚያስፈልጉ የህክምና ቁሳቁሶች ግብዓቶች በሀገር ውስጥ በበቂ ሁኔታ የሚገኙ ባለመሆናቸው በግብዓት እጥረት ምክንያት በሳምንት አራት ቀዶ ጥገናዎች ብቻ ለማድረግ የሚገደዱ እንደሆነ አመላክተዋል።

ማዕከሉ ከተለያዩ ድርጅቶች እና በጎ አድራጊ ግለሰቦች ከሚያገኘው ድጋፍ ባሻገርም በኢትዮ ቴሌኮም በኩል በተዘጋጀው አጭር የጽሁፍ መልዕክት ማንኛውም ህብረተሰብ ድጋፍ እንዲያደርግ የሚያስችል ሥርዓት ተዘርግቷል። በአጭር የጽሁፍ መልዕክት በአንድ ወር ወደ አንድ ሚሊዮን የሚጠጋ ብር መሰብሰብ እንደተቻለ ያስታወሱት ዋና ሥራ አስፈጻሚው፤ ከዚህም ባሻገር ሌሎች የመገናኛ ብዙኃን ነጻ የአየር ሽፋን በመስጠት፣ የማስታወቂያ ሰዓት በመስጠት ማዕከሉን የማገዝ ሥራ የሠሩ መሆኑን አስታውሰው የምስጋና ፕሮግራም መዘጋጀቱን ተናግረዋል።

የልብ ህመም የተያዙ ሰዎች በአሁኑ ሰዓት ቁጥራቸው እየጨመረ መሆኑን ያነሱት ዋና ሥራ አስፈጻሚው ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የሚመጡ ታካሚዎች ሊያሟሉት የሚገባ ቅድመ ሁኔታ ይኖራል? ተብሎ ለቀረበው ጥያቄ ‹‹ሰው መሆኑ እና የልብ ህመም ታካሚ መሆኑ ብቻውን በቂ ነው። ምክንያቱም ድርጅቱን ያቋቋሙት ዶክተር በላይ አበጋዝ በጊዜው ህክምና የሚያስፈልጋቸውን ህጻናት ወደ ሌሎች ሀገራት ወስደው ያሳክሙ ነበር። እነዚያ ሀገራትም በጊዜው ታካሚዎቻችንን ተቀብለው ህክምናውን በነጻ የሚሰጡ ሰው በመሆናቸው ነበር። ማዕከሉ ወደፊትም ከሌሎች ሀገራት ህክምና የሚያስፈልጋቸውን ታካሚዎች ጭምር ተቀብሎ በነጻ የማከም ሃሳብ አለው›› ያሉት ዋና ሥራ አስፈጻሚው ከሌሎች ሀገራት ከኬንያ፣ ኡጋንዳ፣ ማላዊ፣ ሶማሊያ ታካሚዎችን ተቀብሎ በነጻ ከህክምና የመስጠት ጅምሮች እንዳሉም አንስተዋል።

ማዕከሉ የቅድመ ቀዶ-ጥገና እና ድህረ ቀዶ-ጥገና የህክምና ክትትሎችን የሚያደርግ በመሆኑ በየቀኑ ክትትል ሲደረግ ማዕከሉ በሆስፒታሉ ውስጥ ከሚሰጣቸው ህክምናዎች ባሻገር ወደ ማዕከሉ የሚመጡ ታካሚዎችን ከማዕከሉ አቅም በላይ ሲሆንና በፍጥነት ህክምና እንደሚያስፈልገው በህክምና ባለሙያዎች ሲታመንበት ወደ ሌሎች ሀገራት ሄደው እንዲታከሙ ያደርጋል። በሀኪሞች አፋጣኝ ህክምና የሚያስፈልጋቸው መሆኑ ካልተወሰነ በቀር ሁሉም ታካሚዎች ወደ ማዕከሉ በመጡበት የጊዜ ሰሌዳ መሠረት ይስተናገዳሉ። በተጨማሪም ማዕከሉ ህክምና በሚሰጥበት ወቅት የትኛው የልብ ችግር ይታከም የሚለው በማዕከሉ ያለው የህክምና ግብዓት ይወስነዋል ሲሉ ዋና ሥራ አስፈጻሚው ገልጸዋል። በዓመት ውስጥ ከ780 በላይ የሚሆኑ አዳዲስ ታካሚዎች ወደ ማዕከሉ ሪፈር ተጽፎላቸው ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ለህክምና ይመጣሉ።

ማዕከሉ ድጋፍ ከሚያገኝባቸው ተቋማትም ሆኑ ግለሰቦች ባሻገር ከኢትዮቴሌኮም ጋር በጋራ በመሆን በአጭር የጽሁፍ መልዕክት ህብረተሰቡ የሚሳተፍበትን የገቢ ማሰባሰቢያ አማራጭ ፈጥሯል። እንደ ዋና ሥራ አስፈጻሚው ገለጻም በአሁኑ ሰዓት በወር እስከ አንድ ሚሊዮን ብር በዚህ የአጭር የጽሁፍ መልዕክት ይሰበሰባል። ነገር ግን ማዕከሉ ከሚሰጠው አገልግሎት እና ካሉት ታካሚዎች አንጻር ይህም በቂ እንዳልሆነ አንስተዋል። የኢትዮ ቴሌኮም ተግባርም ለሌሎች ተቋማት እንደ ጥሩ ማሳያ መሆኑን አንስተዋል።



# በኦሮሚያ በዘንድሮው አረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

የተለያዩ ለምግብ የሚውሉ የፍራፍሬ ዝርያዎች ናቸው ብለዋል።

ከ2011 ዓ.ም በፊት 17 በመቶ የነበረውን የክልሉ የደን ሽፋን ወደ 27 በመቶ ማሳደግ መቻሉን ጠቅሰው፤ በሀገር አቀፍ ደረጃ አረንጓዴ ኢኮኖሚ ለመገንባት እየተሠራ እንደሚገኝም ጠቁመዋል፡፡

የለውጡ መንግሥት ባለፉት ዓመታት የዜጎችን የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻል በልዩ ትኩረት እየሠራ ነው ያሉት አቶ ሽመልስ፤ ፈተናዎች ሳይበግሩት ለመጪው ትውልድ የተሻለች ሀገር ለማስረከብ የተለያዩ ፕሮጀክቶችን ተግባራዊ እያደረገ ይገኛል ብለዋል።

መንግሥት ሥር የሰደደውን ኋላ ቀርነትና ድህነትን ከስሩ በመንቀል ዜጎችን ወደ ብልጽግና ለማሸጋገር እየሠራ መሆኑን ጠቅሰው፤ ብልፅግናን ለማረጋገጥ ከሕዝብ ጋር በመቀናጀት በልዩ ትኩረት እየተሠራ እንደሚገኝ ገልጸዋል።

ክልሉ ምዕራብ ኦሮሚያን የሠላም የልማትና የብልፅግና ማዕከል ለማድረግ እየሠራ መሆኑን ጠቁመው፤ ሕዝቡ ሠላምን ለማጽናት የጀመረውን ጥረት አጠናክሮ እንዲቀጥል ጥሪ አቅርበዋል።

የኦሮሚያ ክልል የግብርና ቢሮ ኃላፊ አቶ ጌቱ ገመቹ በበኩላቸው፤ በኦሮሚያ በዘንድሮው አረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር አራት ነጥብ 95 ቢሊዮን ችግኝ ይተከላል ብለዋል።

ለመርሐ ግብሩ አምሥት ነጥብ አምሥት ቢሊየን ችግኝ የተዘጋጀ ሲሆን አራት ነጥብ 95 ቢሊዮን ችግኝ እንደሚተከል ገልጸው፤ የችግኝ መትከያ ጉድጓዶች በአንድ ነጥብ ሦስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ላይ መዘጋጀታቸውን ገልጸዋል።

የኦሮሚያ ክልል ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ በአረንጓዴ ዐሻራ ፕሮግራም 18 ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ችግኞችን መትከሉን ጠቅሰው፤ ከዚህ ውስጥ 88 ነጥብ አምሥት በመቶ የሚሆኑት መፅደቃቸውን አስረድተዋል።

አረንጓዴ ዐሻራ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የውሃ ሀብትን ለማሳደግ የደን ሽፋንን ከፍ ለማድረግ እንደሚረዳም አያይዘው ገልዋል፡፡

በመርሐ ግብሩ ላይ ርዕሰ መስተዳድር አቶ ሽመልስ አብዲሳ፣ የገንዘብ ሚኒስትር ዴኤታ ኢዮብ ተካልኝ(ዶ/ር)፣ የኦሮሚያ ብልፅግና ቢሮ ኃላፊ አቶ ፍቃዱ ተሰማን ጨምሮ ከፍተኛ የፌዴራልና የክልል የሥራ ኃላፊዎች ተገኝተዋል።

# ወጣቶች የሀገራቸውን ብዝኃነት በመረዳት ለሀገራዊ ግንባታ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ለመስጠት ከተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች አዲስ አበባ የመጡ የ2ኛና የ3ኛ ዓመት የተማሪዎች አቀባበል የተደረገላቸው ሲሆን የሥራ መመሪያ ተሰጥቷቸዋል፡፡

በማስጀመሪያ መርሐ ግብሩ ላይ ንግግር ያደረጉት የሠላም ሚኒስትር ዴኤታ ኬይረዲን ተዘራ (ዶ/ር) እንደገለጹት፣ ወጣቱ ኢትዮጵያ የብዝኃነት ሀገር መሆኗን ሊገነዘብ ይገባል፡፡ ኢትዮጵያ የብዝኃ ባሕል፣ ቋንቋ፣ ሃይማኖትና የተለያዩ ማንነቶች ያሏቸው ዜጎች ባለቤት ናት፡፡

በተለይ የድንበር ተሻጋሪ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ሰጭ ወጣቶች የሀገራቸውን ብዝኃነት በመረዳት ለሀገር ግንባታ ቁልፍ ሚና ሊወጡ እንደሚገባ ገልጸዋል፡፡

ወጣቱ ትውልድ የነገ ሀገር ተረካቢ በመሆኑ በበጎ ፈቃድ ማኅበረሰብን ማገልገል ይጠበቅበታል ያሉት ኬይረዲን (ዶ/ር)፤ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ከማኅበረሰቡ ጋር ለመግባባትና ብዙ ባሕሎችን ለመረዳት እንደሚጠቅም አብራርተዋል፡፡

የክረምት የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ሰጭ ተማሪዎች ለማኅበረሰቡ ከሚሰጡት አገልግሎት ባሻገር ለሀገራዊ መግባባት ትልቅ ሚና ይኖራቸዋልም ብለዋል፡፡

ኢትዮጵያዊነትን ለማጠናከር ታላቅ ተልዕኮ እንደተቀበሉ በመገንዘብ አስፈላጊውን አገልግሎት መስጠት እንዳለባቸው አሳስበዋል፡፡

የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ማኅበራዊ ግንኙነትን ማጠናከር፣ ሀገርን ለመገንባት አይነተኛ መንገድ መሆኑን የገለጹት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ወሰን ተሻጋሪ የማኅበረሰብ አገልግሎት የተለያዩ ማንነቶችን ለማወቅና ሀገራዊ ፍቅርን ለማሳደግ እንደሚረዳ ገልጸዋል፡፡

አዲስ አበባ የሁሉም ዜጋ መኖሪያ በመሆኗ የተለያዩ ማንነቶችን ለመገንዘብ ትልቅ እድል እንደሚፈጥር ጠቁመው፤ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ሰጪ ተማሪዎች በቆይታቸው አብሮነትንና ኢትዮጵያዊነትን የመገንባት ኃላፊነት እንዳለባቸው ገልጸዋል፡፡ የሚሰጡት የማኅበረሰብ አገልግሎት ያለ ልዩነት መሆን እንዳለበትም መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡

በማስጀመሪያ መርሐ ግብሩ ላይ ንግግር ያደረጉት የአዲስ አበባ ከተማ ሠላምና ፀጥታ አስተዳደር ቢሮ ወይዘሮ ሊዲያ ግርማ፤ አዲስ አበባ ከተማ የዲፕሎማሲ መዲና በመሆኗ ሠላምና ፀጥታ ሊረጋገጥ ይገባል ብለዋል፡፡

የሀገር አቀፍ የበጐ ፈቃድ ሥራዎች ተግባራዊ መደረግ ከተጀመሩበት ጊዜ ጀምሮ በርካታ የማኅበራዊና የሠላም ግንባታ ውጤታማነት መመዝገቡን አብራርተዋል፡፡

እንደ ኃላፊዋ ገለጻ፤ የሀገር አቀፍ አካል የሆነው የዘንድሮው የበጐ ፈቃድ አገልግሎት የሠላምና ፀጥታ፣ አብሮነትንና መግባባትን ለማጠናከር ይረዳል፡፡

የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ተሳታፊዎች ከተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች መውጣጣታቸውን እና በቁጥርም 613 መሆናቸውን ጠቅሰው፤ በአንድ ወር ቆይታቸው ከሠላም ሠራዊት ጋር በመቀናጀት የሠላም እሴት ግንባታ፣ በአካባቢ ፀጥታ አጠባበቅ፣ በእውቀት ሽግግርና ሌሎች ማኅበራዊ በጎ ፈቃድ ሥራዎችን በመሥራት ለሀገራዊ አንድነት ትልቅ አበርክቶ እንደሚኖራቸው ጠቅሰዋል፡፡

# በአዲስ አበባ ነዳጅ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

አራት ኪሎ ቱሪስት ሆቴል ማደያ ላይ ለበርካታ ሰዓታት ወረፋ በመጠበቅ መቆየታቸውን የገለጹት አቶ አማረ፤ ነዳጅ ለመቅዳት ከጠዋቱ አሥራ ሁለት ሰዓት ጀምሮ እስከ ስድስት ሰዓት ድረስ መቆየታቸውን ገልጸዋል።

ጠዋት ወደ ሥራ ቦታቸው መሄድ ሲገባቸው ነዳጅ ለመቅዳት ረጅም ሰዓት መቆየታቸው ችግር ውስጥ ያስገባቸው መሆኑን የተናገሩት አቶ አማረ፤ ችግሩ መንግሥትና ሕዝብ ላይ የሚያሳድረው አሉታዊ ተፅዕኖ ከፍተኛ መሆኑን ጠቁመዋል።

ያለፈው ሳምንት በአዲስ አበባ የነዳጅ ማደያዎች ስፍራ ረጃጅም ሰልፎች እንደነበሩ የተናገሩት አቶ አማረ፤ የሰልፉ መጠን በየቀኑ ይቀንሳል ሲባል ይበልጥ ተጠናክሮ መቀጠሉን ነው የገለጹት።

ወጣት ዳግማዊ የሻለው በበኩሉ፤ ሰሞኑን በነዳጅ እጥረት ሲቸገር መቆየቱን ተናግሯል። በዚህም በርካታ መኪናዎች በነዳጅ ማደያ ስፍራዎች ተሰልፈው ማየቱንና እሱም ተመሳሳይ ዕጣ እንደገጠመው አስረድቷል።

ይህም በከተማዋ የትራንስፖርት ፍሰት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ከማስከተሉ በተጨማሪ የእያንዳንዱን ግለሰብ የሥራ እንቅስቃሴ ጎድቷል ነው ያለው ወጣት ዳግማዊ።

ነዳጅ ለመቅዳት ከጠዋቱ አሥራ ሁለት ሰዓት እስከ አምስት ሰዓት ድረስ መሰለፉን የገለጸው ወጣት ዳግማዊ፤ የሚመለከተው አካል ችግሩን በፍጥነት ሊፈታ እንደሚገባ ገልጿል።

ችግሩ እንዳሳሰባቸው ጠቅሰው፤ ሰሞኑን በአዲስ አበባ ያጋጠመው የመኪኖች የነዳጅ ወረፋ በምን ምክንያት ሊከሰት እንደቻለ የሚመለከተው አካል ሊያሳውቅ ይገባል ያሉት ደግሞ አቶ ቴዎድሮስ ሽፈራው ናቸው።

የነዳጅና ኢነርጂ ባለሥልጣን የሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር በቀለች ኩማ ለኢፕድ በሰጡት ምላሽ፤ በነዳጅ ማደያዎች ረጃጅም የመኪና ወረፋዎች መስተዋላቸውን አምነዋል።

በአዲስ አበባ የነዳጅ ማደያ ስፍራዎች ላይ የሚስተዋለውን ረዣዥም የመኪና ሰልፎች ለመቅረፍ ሰፊ ርብርብ እየተደረገ መሆኑንም ነው የገለጹት።

እንደሀገር በተገቢው ጊዜና ወቅት የነዳጅ ግዢ መፈፀሙን የገለጹት ዳይሬክተሯ፤ ሆኖም ሰሞኑን ጅቡቲ ያለው የነዳጅ ዴፖ እድሳት ላይ በመሆኑ የዴፖው የመቅዳት መጠን መቀነሱን ጠቁመዋል።

የዴፖው እድሳት ላይ መሆን የነዳጅ ጫኝ መኪኖችን ጭኖ ለመውጣት የነበረው የቆይታ ጊዜ በጥቂቱ እንዲረዝም ማድረጉን ገልጸው፤ ይህ በአዲስ አበባ ነዳጅ ማደያዎች ወረፋ እንዲፈጠር ማድረጉን ተናግረዋል።

ችግሩን ለመፍታት ርብርብ እየተደረገ መሆኑን እና ለሀገር ውስጥ ዴፖዎች አስፈላጊውን መጠን ለማሟላት ጥረት እየተደረገ እንደሚገኝም ነው ያስረዱት።

# የኮሪደር ልማቱ ቅርሶችን በማልማት በመዲናዋ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

መዳረሻ ከመሆን ባለፈ አትጎበኝም ነበር ያሉት

ሂሩት (ዶ/ር)፤ አሁን የኮሪደር ልማቱ በመዲናዋ የሚገኙ ቅርሶችን እንዲታደሱና እንዲለሙ ዕድል በመከፈቱ የጎብኝዎቿ ቁጥር ከፍ እንዲል አድርጓል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

የኮሪደር ልማት በመዲናዋ የሚገኙ ቅርሶች ለጉብኝት ምቹ እንዲሆኑ የማደስ፤ የማይታወቁት እንዲታወቁ፣ ያለሙት እንዲለሙ እያደረገ ነው ብለውም፤ ይህም የቱሪስት ፍሰቱን ይበልጥ እያሳደገ ነው ብለዋል፡፡

ቅርሶችን በሚገባቸው ልክ አልምቶ ለቱሪስት ክፍት ማድረግ የመንግሥት ሥራ ብቻ አይደለም ያሉት ሚኒስትሯ፤ ሁሉም ማኅበረሰብ የልማቱ ተካፋይ ሊሆን ይገባል ሲሉ ጠቁመዋል፡፡

የተከፈተው ታሊስማን የስዕል ጋለሪ ለስዕል ባለሙያዎች ምቹ በመሆኑ ብዙ የስዕል አርቲስቶችን ለማፍራት የሚያስችል ነው ሲሉ ገልጸዋል፡፡

ታሊስማን የስዕል ጋለሪ አሁን ካለበት የበለጠ እንዲለማና ከስዕለ ጋለሪነት ባለፈ ለፊልም ኢንዱስትሪው እንዲያገለግል ተጨማሪ ሥራ መሥራት አለበት ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ጋለሪው የተከፈተበት ቦታ ተስማሚ የአየር ፀባይ፤ ሰፊ ግቢ፣ ለጥበበ ሥራ አመች የሆነ የተፈጥሮ ውበት ያለው መሆኑን አያይዘው የጠቀሱት ቢሮ ኃላፊዋ፤ አርቲስቶች ለጥበብ ሥራ ሊጠቀሙበትም ሆነ ሊያለሙት ይገባል ሲሉ ጠቁመዋል፡፡

የጋለሪው ባለቤት አርቲስት ማሲሞ ዴ ቪታ በበኩላቸው፤ የተከፈተው የታሊስማን የስዕል ጋለሪ የመዲናዋን የቱሪትም ፍሰት የሚያሳድግ ነው ሲሉ ገልጸዋል፡፡

ጋለሪው የቱሪስት ፍሰቱን በማሳደግ ለሥራአጥ ዜጎች የሥራ ዕድል ይፈጥራል ብለዋል፡፡

ሰዓሊዎች የሚስሉበት የቦታ ችግር አለ ያለው አርቲስቱ፤ የተከፈተው ጋለሪ ችግሩን ፈትቶ ብዙ የስዕል ባለሙያዎችን ያፈራል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ጋለሪው የኢትዮጵያን የስዕል ዘርፍ የሚሳደግ መሆኑን ተናግረውም፤ የስዕሉን ዘርፍ ለማሳደግ ጋለሪዎችን ማስፋፋት ተገቢ ነው ሲሉ ጠቁመዋል፡፡



ሂሩት ካሣው (ዶ/ር)



ማሲሞ ዴ ቪታ

# ስፖርት





## በአጭር ርቀትና የሜዳ ተግባራት ተስፋ የታየበት የአፍሪካ ሻምፒዮና

**ብርሃን ፈይሳ**

በካሜሮን፣ ዱዋላ ሲካሄድ በቆየው 23ኛው የአፍሪካ አትሌቲክስ ሻምፒዮና ለተሳተፈው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን የዕውቅና መርሐ ግብር ዛሬ ይደረጋል። ትናንት ምሽት ወደ ሃገሩ የገባው ብሔራዊ ቡድኑ 4ኛ ደረጃን በመያዝ ማጠናቀቁ የሚታወቅ ነው። ይህንንም ተከትሎ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በውድድር መድረኩ ሃገራቸውን ለወከሉ አትሌቶች ረፋድ ላይ ዕውቅና የሚሰጥ ይሆናል።

በሩጫ፣ ዝላይና ውርወራ ስፖርቶች ሃገራትን የሚያፎካክረው የአፍሪካ አትሌቲክስ ሻምፒዮና ዘንድሮ በካሜሮን አዘጋጅነት ላለፉት ስድስት ቀናት ሲካሄድ ቆይቷል። ከአህጉሪቷ 27 ሀገራት የተውጣጡና ከ2ሺህ 500 በላይ አትሌቶች የተሳተፉበት ውድድሩ በደቡብ አፍሪካ አጠቃላይ አሸናፊነት ተጠናቋል። ሃገሪቷ 20 ሜዳሊያዎችን መሰብሰቧ ቀዳሚ ያደረጋት ሲሆን፤ ኬንያ በ19፣ ናይጄሪያ ደግሞ በ15 ሜዳሊያዎች ቀጣዮቹን ደረጃዎች ይዘዋል። አራተኛዋ ሃገር ኢትዮጵያም 5 የወርቅ፣ 4 የብር እና 1 የነሃስ በጥቅሉ 10 ሜዳሊያዎችን ማስመዝገብ ችላለች።

እነዚህ ሜዳሊያዎች የተገኙትም ባሳተፈቻቸው 32 ሴት እና በ36 ወንድ፤ በድምሩ 68 አትሌቶች ነው። በዚህ ውድድር ኢትዮጵያ በሩጫና በሜዳ ተግባራት የተሳተፈች ቢሆንም ውጤት የተገኘው ግን በተለመዱት ርቀቶች እና በእርምጃ ብቻ ነው። በዚህም በ5ሺህ እና 10ሺህ ሜትር ርቀቶች የተወዳደረው አትሌት ንብረት መላክ የወርቅ እና የብር ሜዳሊያዎችን በማጥለቅ ቀዳሚው ሆኗል። ልምድ ካላቸው አትሌቶች መካከል የሚመደበው ንብረት ከ5ሺህ እስከ ግማሽ ማራቶን በመሮጥ ይታወቃል። ከወራት በፊት በተካሄደው




የአፍሪካ ጨዋታዎች ላይም በ10ሺህ ሜትር ለሃገሩ የወርቅ ሜዳሊያ ያስመዘገበ ሲሆን፤ ያለፈው ዓመት የሊዝበን ግማሽ ማራቶን ውድድር አሸናፊም ነው።

በወንዶች ምድብ ሁለተኛው የወርቅ ሜዳሊያ ደግሞ በ20 ኪሎ ሜትር እርምጃ በአትሌት ምስጋናው ዋቁማ የተገኘ ነው። ተጨማሪዎቹ የወርቅ ሜዳሊያዎችም በሴቶች 1ሺህ 500 ሜትር በአትሌት ሳሮን በርሄ፣ በ5ሺህ ሜትር ፈንታዬ በላይነህ፤ እንዲሁም በ20 ኪሎ ሜትር እርምጃ ስንታየሁ ማስሬ ተመዝግበዋል። የብር ሜዳሊያዎቹም በ5ሺህ ሜትር በአትሌት ውብርስት አስቻል እና በ3ሺህ ሜትር በአለምናት ዋሌ፤ እንዲሁም በወንዶች 10ሺህ ሜትር በአትሌት ድሪባ ገመቹ በብቸኝነት ተመዝግቧል። ኬንያዎች የበላይነቱን በያዙበት የሴቶች 10ሺህ ሜትር ደግሞ አትሌት ገላ ሃምቢሴ ሦስተኛ ደረጃን በመያዝ ብቸኛውን የነሐስ ሜዳሊያ ለሃገሯ አስገኝታለች።

በዚህ ውድድር ከተሳተፉት አብዛኛዎች አትሌቶች ወጣቶች ሲሆኑ፣ በዓለምና አሕጉር አቀፍ ውድድሮች ልምድ በመቅሰም ላይ የሚገኙና በቀጣይም ታላላቅ የውድድር መድረኮች ላይ ሃገራቸውን ይወክላሉ በሚል ተስፋ የተጣለባቸው ናቸው። በተወሰኑ ርቀቶች ውጤት ማስመዝገብ ባይቻልም ኢትዮጵያ በታወቀችባቸው የረጅም ርቀት ውድድሮች ላይ ግን እንደተለመደው ሜዳሊያዎች ተመዝግበዋል። በሌሎች የውድድር ዓይነቶች ደግሞ በርካታ ዲፕሎማዎች የተመዘገቡ መሆኑን ከፌዴሬሽኑ የተገኘው መረጃ ይጠቁማል።

ዲፕሎማዎች የተገኙባቸውና ማጣሪያውን አልፈው የፍጻሜ ፉክክር ውስጥ መግባት የተቻለባቸው ውድድሮችም ኢትዮጵያ እምብዛም የማትታወቅባቸው የአጭር ርቀት አትሌቲክስ፤ እንዲሁም የሜዳ ተግባራት ናቸው። ይኸውም በስፖርቱ ወደ ስኬት የመጠጋት ተስፋን የሚያንጸባርቅ በመሆኑ በምን መልኩ ሊሠራበት ይገባል የሚለውን ለፌዴሬሽኑም ሆነ ለስፖርቱ ባለሙያዎች አቅጣጫ ያስቀመጠ ነው። የኢትዮጵያ የዘንድሮው የሻምፒዮናው ተሳትፎዋ በበርካታ ስፖርቶች መሆኑ በአጭር ርቀት ሩጫ፣ ዝላይ፣ ውርወራ እና እርምጃ የሚሳተፉ አትሌቶች ዓለም አቀፍ የውድድር ልምድ የሚያገኙበትን ዕድል የፈጠረላቸው ከመሆኑ ባለፈ ያሉበትንም ደረጃ የሚገመግሙበት ነው። በመሆኑም ተሳትፎው በተለያየ አቅጣጫ ስፖርቱን የሚጠቅምና ለወደፊትም መሰል ውድድሮች ላይ በስፋት መካፈል ያለውን ጠቀሜታ ያመላከተ ነው ሊባል ይችላል።

የአፍሪካ አትሌቲክስ ሻምፒዮና እአአ ከ1979 አንስቶ በየሁለት ዓመቱ የሚደረግ ውድድር ነው። በአፍሪካ አትሌቲክስ ኮንፌዴሬሽን የሚመራው ይህ ውድድር በየመሐሉ ወቅቱን ሳይጠብቅ የሚካሄድ ቢሆንም ዘንድሮ 23ኛው ላይ ደርሷል። እአአ በ2008 ሻምፒዮናውን የማስተናገድ ዕድል ገጠሟት የነበረችው ኢትዮጵያም ከመድረኩ በሰበሰበቻቸው ሜዳሊያዎች በሜዳሊያ ዘንጠረዡ 6ኛ ደረጃ ላይ ልትቀመጥ ችላለች። ናይጄሪያ፣ ኬንያ፣ ደቡብ አፍሪካ፣ አልጄሪያ እና ሞሮኮም ከአንድ እስከ አምስት ያሉትን ደረጃዎች ይዘዋል።